በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የቀረጥ ነጻ ንግድ አሰራርናአፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ታህሳስ 2005 ዓ.ም
አዲስ አበባ

ማውጫ

ገጽ

ክፍል አንድ 1
መግቢያ 1
ባለሥልጣን መ/ቤቱ አመሰራረት፤ 1
የባለሥልጣኑ ዓላማዎች 2
የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር፤ 2
የባለስልጣን መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ እና መዋቅር፤ 4
የኦዲቱ ዓላማ 5
የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ፤ 5
የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርት፤ 5
የኦዲቱ ወሰን፤ 5
የኦዲቱ ዘዴ፤ 6
ከቀረጥ ነጻ ንግድ አሠራርና አፈጻጸም የሚመለከታቸው የስራ ሂደቶች፤ 6
ክፍል ሁለት 8
ግኝቶች.. 8
፩. የቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ሥራ ፈቃድ ፣ በውጭ ምንዛሪ መገበያየት የሚያስችል ፈቃድ እና የመጋዘን ፍቃድ አሰጣጥን በተመለከተ፡- 8
የቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ሥራ ፈቃድ አሰጣጥና እድሳት ወጥ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ስለመደረጉና ውጤታማ ስለመሆኑ፤ 8
ከቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ሥራ ላይ ለተሰማሩ የግል ድርጅቶች በውጭ ምንዛሪ ለመቀበል የሚያስችል ፈቃድ አሰጣጥና እድሳት ተግባራዊ ስለመደረጉ፣ 11
በቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ድርጅቶች የግል የዕቃ ማከማቻ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ አሰጣጥና እድሳትን በተመለከተ፤ 13
የግል ዕቃ ማከማቻ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ ለግል የቀረጥ ነጻ ድርጅቶች ስለመሰጠቱ፡- 14
የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን እድሳትን በተመለከተ፡- 16
የቀረጥና ታክስ ነፃ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን የፈቃድ አሰጣጥ በመመሪያ መሠረት ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ 17
ወደ መጋዘን በገቡ እቃዎች ላይ ስርቆት የተፈጸመ ከሆነ የመጋዘን ፈቃድ እስከ መሰረዝ መድረሱን በተመለከተ 18
በመጋዘን ውስጥ ስርቆት በሚፈጸምበት ወቅት እርምጃ ስለመወሰዱ፡- 19
፪. ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሚፈጸምባቸው መሆኑ በተመለከተ 20

ከቀረጥና ታክስ ነፃ ዕቃዎች ወደ ቀረጥ ነፃ ሱቅ ከመግባተቸው በፊት የዕቃዎቹ ዝርዝር መረጃ በጉምሩክ መያዙን በተመለከተ 20
ከቀረጥና ታክስ ነጻ ወደ ሀገር የገቡ ዕቃዎች መረጃ በተመለከተ 21
ወደ ጉምሩክ መጋዘን የሚገባ ዕቃ የሚመዘገብበት ስርዓት ስለመኖሩ፡- 22
በፍተሻ ወቅት የተገኘ ልዩነት ስለመተላለፉ፡- 22
፫. ለቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ስራ መመሪያና የአሠራር ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ 23
በቀረጥ ነፃ ሱቆች ውስጥ ጊዜ ያለፈባቸውና በሚጓጓዙበት ወቅት ጉዳት ለደረሰባቸው ዕቃዎች ለማስወገድ የአፈፃፀም መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ስለመደረጉ 23
የቀረጥና ታክስ ነጻ ዕቃዎች ሽያጭ አፈጻጸምን በተመለከተ 25
፬.የቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ አሰራርን በተመለከተ 26
፭.የቀረጥ ነፃ ዕቃዎች ሽያጭ ሂደትና የጉምሩክ ክትትልና ቁጥጥር ውጤታማ መሆኑን ማጣራት.. 26
ከቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች የሽያጭ ሪፖርት በየወሩ ጉምሩክ በመቀበል ትክክለኝነቱ መረጋገጥ እና ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ 26
የቀረጥ ነጻ ዕቃዎች ሽያጭ ትክክነኝነቱ ስለመረጋገጡ፡- 28
የዓለም አቀፍ መንገደኞችን ስም ዝርዝር ከአጓጓዥ ድርጅቶች በመቀበል ለባለመብቶች ብቻ ሽያጭ ስለመፈጸሙ 29
በቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት ወደ ሀገር ያስገቧቸው ዕቃዎችን የሚያከማቹበት መጋዘኖችና ሱቆች ውስጥ የገባ ዕቃ መረጃ መያዙን እና ክትትልና ቁጥጥርን በተመለከተ 29
በቦንድድ መጋዘን እና በመደብሮች ላይ ቆጠራ ስለመደረጉ 30
ክፍል ሦስት 32
መደምደሚያ 32
ክፍል አራት 35
የማሻሻያ ሀሳቦች 35

አባሪዎች

አባሪ 1 የኦዲት መመዘኛ መስፈርት የገጽ ብዛት 3
አባሪ-2 በኦዲቱ የታዩ መ/ቤቶች እና ድርጅቶች ዝርዝር የገጽ ብዛት 1
አባሪ-3 ቃለ መጠይቅና መጠይቅ የቀረበላቸው አካላት የገጽ ብዛት 2
አባሪ 4 የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ድርጅታዊ መዋቅር የገጽ ብዛት 1
አባሪ 5 በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የተሰበሰበ ገቢ እና የተመደበ በጀት የገጽ ብዛት 2
አባሪ 6 የቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ በሚመለከታቸው የስራ ሂደቶች ስር ያሉ ንዑስ የስራ ሂደቶች ዝርዝር የገጽ ብዛት 2
አባሪ 7 የቀረጥ ነጻ ንግድ አሠራርና አፈጻጸም የአሠራር ሥርዓት ትንተና (System Description) የገጽ ብዛት 1

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የቀረጥ ነጻ ንግድ አሠራርና አፈጻጸምን በተመለከተ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ክፍል አንድ

መግቢያ

1. የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት ወሳኝ ሚና ያለው ሲሆን፣ ገቢውንም የሚሰበስበው ወደ ሀገር ከሚገቡ፣ ከሀገር ከሚወጡ ዕቃዎች ላይ ከሚጣል ቀረጥና ታክስ እንዲሁም ከሀገር ውስጥ ከተለያየ አይነት ታክስ (ግብር) ነው፡፡ ቀረጥና ታክስ ነጻ ማለት ዕቃዎች ከውጭ ሲገቡ፣ መንግስት መሰብሰብ የሚገባውን ገቢ በመተው የሀገሪቱን ገጽታ ለመገንባት የተዘረጋ ስርዓት ሲሆን፣ የመብቱ ተጠቃሚዎችም የሀገራት ተወካዮች፣ የአለም አቀፍ ድርጅት ሰራተኞች፣ ወጪና ገቢ አለም አቀፍ መንገደኞች ናቸው፡፡

2. ኦዲቱ እንዲከናወን ያስፈለገበት ምክንያት የህዝቡ ፍላጎት(Public interest) በመሆኑ እና ኦዲቱ እንዲከናወን ከተለያዩ አካላት ጥያቄ በመምጣቱ ሲሆን፣ የመግቢያ ውይይት በተደረገበት ወቅት ኦዲቱ ቢሰራ ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ፍላጎት ያለው መሆኑን በመግለጹ ነው፡፡

3. በደሰሳና በቅኝት ኦዲቱ ውጤት መሰረት የኦዲት ቡድኑ በባለስልጣን መ/ቤቱ የሚከናወኑ ሁለት (2) ስራዎችን /የቀረጥ ነፃ ንግድ አሰራርና አፈጻጸም እና ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት የተዘረጋ የታክስ ማበረታቻ ሥርዓት አፈጻጸም ብቃት ያለውና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ/ የሚሉትን በመገምገም የክዋኔ ኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችን/የኦዲት አካባቢዎችን በመለየት እና ከሁለቱ የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ውስጥ የተለያዩ የመምረጫ መስፈርቶችን በመጠቀም "የቀረጥና ታክስ ንግድ አሰራርና አፈጻጸም" የሚለው ተመርጦ ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በአዲስ አበባ ኤርፖርት ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሲሆን፣ ሶስት የግል ሱቆች እና ሁለት የመንግስት ድርጅቶችን የሚዳስስ ይሆናል፡፡

የባለሥልጣን መ/ቤቱ አመሰራረት፤

4. በ1989 ዓ.ም. በአዋጅ ቁጥር 60/1989 የፌዴራል መንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን በመባል እንደገና የተቋቋመ ሲሆን፣ ተጠሪነቱም ለገቢዎች ቦርድ እንዲሆን ተደነገገ፡፡ ከዚያም በአዋጅ ቁጥር 368/1995 የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ተጠሪነቱ ለገቢዎች ሚኒስቴር ሆነ፡፡ በመቀጠልም በአዋጅ ቁጥር 587/2000 የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣንን በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ "የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን" ተብሎ እንዲቋቋምና ባለስልጣን መ/ቤቱ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲሆን ተደንግጓል፡፡ በዚሁ አዋጅ ላይ ብቁ ባለሙያዎችን ያቀፈ የባለስልጣኑ አማካሪ ቦርድ

እንደሚቋቋም፣ የቦርዱ ሊቀመንበር ዋና ዳይሬክተሩ እንደሚሆኑ፣ የአባላቱ አሰያየም ችሎታና ብቃትን መሠረት በማድረግ በዋና ዳይሬክተሩ መሆኑን፣ የቦርዱ ዋና ፀሀፊም በዋና ዳይሬክተሩ እንደሚመደብና ቦርዱም በዕለት ተዕለት ተግባሮች ላይ ሳይገባ ባለሥልጣኑን በፖሊሲና ስትራቴጂ ነክ ጉዳዮች ላይ እንደሚያማክር የተገለጸ ቢሆንም፣ እስከ አሁን ተቋቁሞ ሥራ ያልጀመረ መሆኑ ታውቋል፡፡

5. በመጨረሻም ቀልጣፋና ዘመናዊ የጉምሩክ ሕግ ማዕቀፍ በማስፈለጉ እና ሀገሪቱ የፈረመቻቸው አለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊና አካባቢያዊ የንግድ ስምምነቶች ወቅታዊ ሕግና የአሠራር ሥርዓት እንዲኖር የሚያስገድዱ በመሆናቸው በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ "የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001" ታውጇል፡፡

6. በመስከረም ወር 2003 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መካከል በተደረገው የሁለትዮሽ ስምምነት መሠረት በከተማው የሚሰበሰበውን ገቢ አስመልክቶ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኃላፊነት በከተማው አስተዳደር የሚሰበሰበውን ገቢ የመሰብሰብ እና የታክስ አስተዳደር ሥልጣኑን ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በውክልና አስተላልፏል፡፡

የባለሥልጣኑ ዓላማዎች

7. በአዋጅ ቁጥር 587/2000 መሰረት የባለሥልጣኑ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ዘመናዊ የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት በመዘርጋት ለተገልጋዮች ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት፣
- ታክስ ከፋዩ ግዴታውን በፈቃደኝነት እንዲወጣ ማስቻል፣
- ኮንትሮባንድንና የታክስ ማጭበርበርና ስወራን በመከላከልና በመቆጣጠር የታክስና የጉምሩክ ሕግጋትን ማስከበር፣
- ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን የታክስ ገቢ በብቃትና በወቅቱ መሰብሰብ፣
- የፌዴራልና የክልል ታክስ አስተዳደር ሥርዓቶች የተጣጣሙ እንዲሆኑ ለማድረግ ለክልሎች አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፡፡

የባለሥልጣኑ ሥልጣንና ተግባር፤

8. ባለስልጣኑ በአዋጅ ቁጥር 587/2000 የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፡፡

- ዘመናዊ የገቢ አወሳሰንና አሰባሰብ ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ያደርጋል፡:
- በመስኩ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን መሠረት በማድረግ ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ይሰጣል፤ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት ለባለሀብቶች የተሰጡ

የታክስና የቀረጥ ነፃ መብቶች በአግባቡ እንዲፈፀሙ ያደርጋል፤ ለታሰበው ዓላማ መዋላቸውን ይከታተላል፡፡

- ታክስ ከፋዮች በፈቃደኝነት ታክስ የመክፈል ባሕልን እንዲያዳብሩ የግንዘቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ያደርጋል፣
- የታክስ ማስከፈያ ዋጋ ይተምናል፤ ተከፋይ የሚሆነውን የታክስ መጠን ይወስናል፤ ይሰበስባል፣
- የጉምሩክና የታክስ ሕጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን አፈፃፀም ለማሻሻል የበለጠ አጽንኦት በመስጠትና ሌሎች ገቢዎች በአግባቡ እንዲሰበሰቡ ለማድረግ የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ያካሂዳል፣ በጥናትና ምርምሩ ውጤት መሠረት ፖሊሲዎችንና ህጎችን ያመነጫል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣
- ለገቢና ወጪ ዕቃዎች ቁጥጥርና ለታክስ አወሳሰን የሚያስፈልጉ መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ይተነትናል፣ በመስኩ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች የተሟላ የእስታትስቲክስ መረጃ ያጠናቅራል፤ እንደ አስፈላጊነቱም ለሌሎች አካላት ያሰራጫል፣
- የሠራተኞችን አቅም ለመገንባት የሚያስችለውን ማዕከል እንዲደራጅ ያደርጋል፤ የስልጠናና የሙያ መሻሻያ ሥርዓቶችን ይዘረጋል፣
- በጉምሩክ ወደቦች፣ በወሰን አካባቢዎች እንዲሁም በሌሎች የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎችና ማቋረጫ መሥመሮች በኩል የሚገቡና የሚወጡ ዕቃዎችንና ማጓጓዣዎችን ይፈትሻል፣ የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ተፈጽሞባቸው መግባታቸውንና መውጣታቸውን ያረጋግጣል፣
- ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ወደ አገር የሚገቡትን ወይም ከአገር የሚወጡትን እቃዎች እንቅስቃሴ የመቆጣጠርና ኮንትሮባንድን የመከላከል ሥራ በፌዴራል ፖሊስ አማካኝነት እንዲካሄድ የመረጃ ልውውጥ ያደርጋል፤ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፤ ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት ተገቢውን እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፣
- የጉምሩክና የታክስ ሕጎችን በመጣስ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ይመረምራል፤ ይከሳል፣ ይከራከራል፤ ይህንኑ ለማከናወን የራሱን ዐቃቤያነ ሕግና መርማሪዎች ቡድን ያደራጃል አፈፃፀማቸውን ይቆጣጠራል፣

- የጉምሩክና የታክስ ሕጎችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ በማናቸውም ሰው እጅ የሚገኙ ሠነዶችን ይመረምራል፤ ይይዛል፤ ዘመናዊ የዕቃዎችና የሠነዶች ምርመራ አገልግሎት ላብራቶሪ ያደራጃል፤ በጥቅም ላይ ያውላል፣

- ወደ አገር የሚገቡ ወይም ወደ ውጭ አገር የሚላኩ ዕቃዎች የሚከማቹበትን ሥፍራ ይወስናል፤ መጋዘን ያቋቁማል፤ የመጋዘን ፈቃድ ይሰጣል፤ የቀረጥ ነፃ ዕቃዎች መሸጫ መደብሮችን ይቆጣጠራል፤ ስለዕቃዎች አያያዝና ጥበቃ ቁጥጥር ያደርጋል፤ የሰጠውን የመጋዘን ፈቃድ ያግዳል፤ ይሰርዛል፤ የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፣

- በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ የጉምሩክና የታክስ ወንጀሎችን የመመርመር፤ የመክሰስና ኮንትሮባንድን የመቆጣጠር እንዲሁም ታክስ የመወሰንና የመሰብሰብ ሥልጣኑን በሙሉ ወይም በከፊል ለክልል የፍትህ አካላትና ገቢ ሰብሳቢ አካላት በውክልና ሊሰጥ ይችላል፤ ለአፈፃፀሙ ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣

- የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ሥራዎችን በበላይነት ይመራል፤ ይቆጣጠራል፣

- ለክልል ገቢ ሰብሳቢ አካላት ተገቢውን የአቅም ግንባታ ድጋፍ በመስጠት የፌዴራልና የክልል ታክስ አስተዳደር ሥርዓቶች የሚጣጣሙበትን ሁኔታ ይፈጥራል፣

- የታክስና የጉምሩክ አስተዳዳርን በሚመለከት ውሎችንና ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ያደርጋል፣

- በሥራ ላይ ባሉ ሌሎች ሕጎች ለፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣንና ለጉምሩክ ባለሥልጣን ተሰጥተው የነበሩ ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያውላል፣

- የንብረት ባለቤት ለመሆን፤ ውል ለመዋዋልና በስሙ ለመክሰስና ለመከሰስ ይችላል፣

- ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

የባለስልጣን መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ እና መዋቅር፤

9. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መስሪያ ቤት በአንድ ዋና ዳይሬክተር የሚመራ እና አምስት ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች ያሉት ሲሆን ከመንግስት ለደመወዝ፣ ለሥራ ማስኬጃና ካፒታል በጀት ይመደብለታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ባለስልጣኑ ከውጭ ንግድ ቀረጥና ታክስ (ከወጪ እና ገቢ ንግድ ዕቃዎች)፣ ከሀገር ውስጥ ንግድ፣ የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር የተጣራ ትርፍ እና ከኮንትሮባንድ ዕቃዎች ሽያጭ ገቢ ይሰበስባል፡፡ ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የተመደበ በጀት እና በባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የተሰበሰበ ገቢ በአባሪ 5 የሚታይ ሲሆን የባለስልጣን መ/ቤቱ መዋቅር በአባሪ 4 የተያያዟል

የኦዲቱ ዓላማ

10. በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን መ/ቤት የቀረጥ ነጻ ንግድ አሠራርና አፈጻጸም በመመሪያው መሠረት እየተሰራ መሆኑን፣ ለቀረጥ ነጻ ድርጅቶች የንግድ ፈቃድ፣ በውጭ ምንዛሪ መቀበል የሚያስችል ፈቃድ እና የቦንድድ መጋዘን ፈቃድ ከሚመለከታቸው ፈቃድ ሰጪ አካላት እንዳላቸው፣ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት የግል ድርጅቶች የቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ ላይ ለመሰማራት የሚያስችል ህግ መኖሩን፣ የቀረጥ ነጻ ሱቆች ከውጭ ዕቃ ሲያስገቡ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሚፈጸም መሆኑን፣ የቀረጥ ነጻ ሱቆች ከቀረጥና ታክስ ነጻ ያስገቧቸውን ዕቃዎች ሽያጭ የሚያከናውኑበት መንገድ ግልጽና ተጠያቂነትን በሚያሰፍን መልኩ መሆኑን ለማረጋገጥ የተዘጋጀ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋቱን እና በተዘጋጀው መመሪያ መሰረት ተግባራዊ መሆኑን ማረጋገጥ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በባለመብቶች ዙሪያ መደበኛ የሆነ ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን፣ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓትና ግንኙነት መኖሩን፤ የተዘጋጁ መመሪያዎችና የተዘረጉ ሥርዓቶች ውጤታማ መሆናቸውን በመገምገም በአሠራርና በአፈጻጸም የሚታዩ ችግሮች ካሉ መንስዔዎቻቸውን በመለየት የማሻሻያ ሃሳብ ለማቅረብ ነው።

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ፤

11. ከላይ የተገለጸውን የኦዲት ዓላማ ለማከናወን የሚያስችሉ ሶስት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ተቀምጠዋል፡፡ እነሱም፡-

1. በባለስልጣኑና በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ተቆጣጣሪነት የሚከናወኑ የቀረጥ ነፃ ንግድ ሥራ ፣ በውጭ ምንዛሪ ለመቀበል የሚያስችል ፈቃድ እና የመጋዘን ፈቃድ አሰጣጥን በተመለከተ ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ
2. ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም በብቃት እየተከናወነ መሆኑንና የመረጃ ልውውጥ ሥርዓትና ግንኙነት መኖሩን ማጣራት እና
3. የቀረጥና ታክስ ነፃ ዕቃዎች ሽያጭ ሂደትና የጉምሩክ ክትትልና ቁጥጥር ውጤታማ መሆኑን ማጣራት የሚሉ ናቸው፡፡

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች፤

12. ከላይ የተጠቀሱትን ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችን ኦዲት ለማድረግ እንዲያስችል 34 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ተዘጋጅተው ባለስልጣኑ አስተያየት ተሰጥቶባቸዋል፡፡ የተዘጋጁት መመዘኛ መስፈርቶች ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዘዋል፡፡

የኦዲቱ ወሰን፤

13. መ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ኦዲቱ በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች (Ethiopian Performance Audit Standards) የተከናወነ ነው፡፡ ዝርዝር

ኦዲቱ የሚሸፍነው ያለፉትን ሶስት በጀት ዓመታት (ከ2002 እስከ 2005 ዓ.ም የመጀመሪያ ሩብ አመት) ድረስ ነው፡፡ ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መስሪያ ቤት ሲሆን፣ በዋነኛነት በአዲስ አበባ ኤርፖርት በሚገኘው የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ነው፡፡ በተጨማሪም በአዲስ አበባ ኤርፖርት ውስጥ የሚገኙ የግል የቀረጥና ታክስ ነጻ ድርጅቶች፣ የመንግስት ቀረጥ ነጻ ሱቆች፣ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ (ጊዎን እና ሂልተን)ሆቴሎች፣ በአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን (ECA) ግቢ ውስጥ የሚገኙ የቀረጥ ነጻ ሱቆችን እና የኢትዮጵያ አየር መንገድ (በረራ ወቅት ለመንገደኞች ከቀረጥና ታክስ ነጻ ዕቃዎች ሽያጭ ስለሚያከናውን) ናቸው፡፡እንዲሁም የተለያዩ ባለድርሻ አካላት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ንግድ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ምልከታ የተደረገባቸው አካላት ናቸው፡፡(በኦዲቱ የታዩ መ/ቤቶች እና ድርጅቶች ዝርዝር በአባሪ 2 ተያይዘዋል፡፡

የኦዲቱ ዘዴ፤

14. ዝርዝር ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ በአዲስ አበባ ኤርፖርት በሚገኘው የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በተገኙ የቀረጥ ነጻ ንግድ አሠራርን የሚመለከቱ የተለያዩ መረጃዎችን በመከለስ፣ እንዲሁም በአዲስ አበባ ኤርፖርት ውስጥ የሚገኙ የግልና የመንግስት ቀረጥ ነጻ ሱቆች፣ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኙ ሆቴሎች እና በአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን (ECA) ግቢ ውስጥ የሚገኙ የቀረጥ ነጻ ሱቆችን እና የኢትዮጵያ አየር መንገድ በውጭ አገር በረራ ወቅት ለመንገደኞች ከቀረጥ ነጻ የሚሸጡ ዕቃዎች ሽያጭ ላይ የተከናወኑ ሥራዎችን በተመለከተ የሥራ ጉብኝት በማድረግና ተያያዥ የሆኑ ማስረጃዎችን ጠይቆ በመከለስ ነው፡፡

15. ከዚህ በተጨማሪ ከቀረጥ ነጻ ንግድ አሠራር ጋር ግንኙነት ያላቸው ባለድርሻ አካላት (ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ንግድ ሚኒስቴር፣ ኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት እና ኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ…) ለሚገኙ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ ከነዚህ መስሪያ ቤቶች የተለያዩ ማስረጃዎችን በመጠየቅና መከለስ እንዲሁም ሥራው በሚከናወንበት ቦታ በአካል በመገኘት የሥራ ጉብኝት ተደርጓል፡፡ በኦዲቱ ወቅት ቃለ-መጠይቅ/መጠይቅ የቀረበላቸው ባለድርሻ አካላትና በአባሪ 3 የተከለሱ መረጃዎች አባሪ 8 ሆነው ተያይዘዋል፡፡

ከቀረጥ ነጻ ንግድ አሠራርና አፈጻጸም የሚመለከታቸው የስራ ሂደቶች፤

16. የቀረጥ ነጻ ንግድ አሰራርና አፈጻጸምን በተመለከተ ዋናው መ/ቤት ይከናወን የነበረ ሲሆን፣ በአሁን ወቅት በመዋቅሩ መሠረት ሙሉ ክንውኑና አፈጻጸሙን ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ያስተላለፈ በመሆኑ፤ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በስሩ ስድስት (6) የስራ ሂደቶች ያሉት ሲሆን፣ ከነዚህ ውስጥ የሚከተሉት የስራ ሂደቶች፡-

- የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም የሥራ ሂደት፣
- ህግ ማስከበር የሥራ ሂደት፣
- መንገደኞች ጓዝ የሥራ ሂደት፣
- ደንበኞች አገልግሎትና ድጋፍ የሥራ ሂደት እና
- ድህረ ዕቃ አወጣጥና ኦዲት የሥራ ሂደት፡

የቀረጥ ነጻ ንግድ አሰራርና አፈጻጸም ሥራ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸው ናቸው፡፡ በሥራ ሂደቶቹ ስር ያሉ ንዑስ የሥራ ሂደቶች የሚያመለክት ዝርዝር በአባሪ 6 ተያይዟል፡፡

የቀረጥ ነጻ ንግድ አሠራርና አፈጻጸም

የአሠራር ሥርዓት ትንተና (System Description) ፤

17. የቀረጥ ነጻ ንግድ አሠራርና አፈጻጸም የአሠራር ሥርዓት ትንተና (System Description) በአባሪ 7 ተያይዟል፡፡

ክፍል ሁለት

ግኝቶች

፩. የቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ሥራ ፈቃድ ፣ በውጭ ምንዛሪ መገበያየት የሚያስችል ፈቃድ እና የመጋዘን ፍቃድ አሰጣጥን በተመለከተ፡-

የቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ሥራ ፈቃድ አሰጣጥና እድሳት ወጥ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ስለመደረጉና ውጤታማ ስለመሆኑ፤

18. በቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ስራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልጉ አካላት፣ ሥራው ላይ ከመሰማራት በፊት የቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ ሥራ ፈቃድ ማውጣትና በወቅቱ ማደስ ይኖርባቸዋል፡፡

19. በኦዲቱ ወቅት በቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ስራ ላይ ተሰማርተው በመስራት ላይ የሚገኙት የግል የቀረጥ ነጻ ድርጅቶች በቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ስራ ላይ ለመሰማራት የሚያስችል የህግ መሰረት እና የቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ ሥራ ፈቃድ የሌላቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

20. ስለሁኔታው ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በቀረበው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact sheet) ላይ በተሰጠው አስተያየት፣ "የቀረጥ ነጻ መደብር ለማንቀሳቀስ ከቀድሞ ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የአስመጪነት የውጭ ንግድ ሥራ ፈቃድ፣ ከክልል ንግድ ኢንዱስትሪና ቱሪዝም ቢሮ የችርቻሮ ንግድ ሥራ ፈቃድ ያለው እና በተለይም በአለም አቀፍ የአየር ማረፊያ ተርሚናል ውስጥ የቀረጥ ነጻ መሸጫ መደብር /ሱቅ/ ለማግኘት የቻለ በመስኩ እንዲሰማራ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ በተጻፈልን ደብዳቤ መሰረት የተፈቀደላቸው ሥራውን በማከናወን ላይ መሆናቸው" ተገልጿል፡፡

21. ይሁን እንጂ በአዲስ አበባ ቦሌ አለም አቀፍ ኤርፖርት አስተዳደር ጥር 1994 ዓ.ም ለተገልጋይ ኅብረተሰብ በኪራይ የሚሰጡ ልዩ ልዩ ይዞታዎች አጠቃቀም ሥልት ጥናት ላይ በICAO(International Civil Aviation Organization) የተደነገጉ የኤርፖርት የገቢ ማስገኛ ሥራዎች ውስጥ መንግስታዊ በሆኑ ድርጅቶች ብቻ የሚከናወኑ ተብለው የተቀመጡ (የኢሚግሬሽን ስራ፣ የጉምሩክ ስራ እና የቀረጥ ነጻ ንግድ ስራ) መሆናቸው ተጠቅሷል፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ ሲቪል አቬሽን ባለስልጣን መ/ቤት ሰኔ 26,1994 ዓ.ም በኢትዮጵያ ሔራልድ ጋዜጣ ቁጥር 248 ባወጣው የጨረታ ማስታወቂያ ላይ የቀረጥ ነጻ መደብር ሱቅ በሚል ያወጣ ሲሆን፣ ለጨረታው ነጥብ መስጫ ከነበሩ መስፈርቶች ውስጥ አጠቃላይ መስፈርት እና ቴክኒካል መስፈርት ናቸው፡፡

22. አጠቃላይ መስፈርት ተብሎ የተቀመጠው ተጫራቾች ለቴክኒካልና ለፋይናንሻል ምዘና ከማለፋቸው በፊት ማሟላት የሚጠበቅባቸው መስፈርቶችን የያዘ ነው፡፡ ከጠቅላላ መስፈርት

ውስጥም አንደኛው ተጫራቾች አግባብ ያለው ህጋዊ የቀረጥ ነጻ ፈቃድ ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ሆኖ ሳለ በዘርፉ ለመሰማራት የሚያስችል የህግ መሰረት እና የቀረጥ ነጻ ንግድ ፈቃድ ሳይኖራቸው እንዲጫረቱ ተደርጓል፡፡

23. በተጨማሪም በዘርፉ ልምድ ሳይኖራቸው ከአስር ዓመት በላይ እንዳላቸው ተደርጎ ከተወዳዳሪያቸው (37 ዓመት ልምድ ካለው መንግስታዊ የልማት ድርጅት) እኩል 14 ነጥብ በመስጠት ጨረታውን እንዲያሸንፉ በማድረግ ለፈቃድ ሰጪ አካላት(ለቀድሞው የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር፣ ለቀድሞው የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ) ተገቢው የቀረጥ ነጻ ፈቃድ እንዲሰጣቸው የኢትዮጵያ ሲቪል አቬሽን ባለስልጣን በተደጋጋሚ በደብዳቤ በጠየቀው መሰረት ከዛሬ 10 ዓመት በፊት አንደኛው የግል ድርጅት በዘርፉ እንዲሰማራ እድል በመክፈት ቀሪዎቹም(ሁለት የግል ድርጅቶች) በዚሁ አግባብ ሊስተናገዱ ችለዋል፡፡

24. በወቅቱ(የተርሚናሉ ግንባታ በተጠናቀቀበት ወቅት) በሀገሪቱ ያሉትን ህጎች በመፈተሽ ተገቢው አስተዳደርና የቁጥጥር ስርዓት በመዘርጋት የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ደህንነት ከማስጠበቅ እና ተገቢው የፋይናንስ ስርዓት እንዲኖር ለማስቻል የተሰራ ስራም ሆነ የተጠና ጥናት አለመኖሩም በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

25. በኢትዮጵያ ሲቪል አቬሽን ባለስልጣን መ/ቤት የበላይ ኃላፊዎች በቀረጥ ነጻ ንግድ ላይ ለመሰማራት የህግ መሰረት እንደሌለ እየታወቀ እና በዘርፉ ለመሰማራት የሚያስችል ፈቃድ ሳይኖራቸው ያለአግባብ ጨረታውን እንዲሳተፉና እንዲያሸንፉ በማድረግ በቀጣይ ለፈቃድ ሰጪ አካላት የህግ መሰረት ባለመኖሩ ፈቃድ መስጠት እንደማይችሉ በሚገልጹበት ወቅት በተደጋጋሚ ድጋፍ እንዲደረግላቸው በደብዳቤ በመጠየቅ በዘርፉ እንዲሰማሩ እንደተደረገ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

26. በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር 67/1989 እና 686/2003 መሠረት የቀድሞው የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መ/ቤት የንግድ ሥራ ፈቃድ የሚሰጥባቸው የንግድ ሥራ ዘርፎች ዝርዝር ውስጥ የቀረጥ ነጻ ንግድ ዘርፍ ሳይካተት፣

- በሚኒስቴር መ/ቤቱም በቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ስራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልጉ አካላት ማሟላት የሚገባቸው መስፈርት ሳይዘጋጅ፣
- በወቅቱ በገቢዎች ሚኒስቴርና በኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን በኩልም የሚያስፈልገውን በቂ የሰው ሀይል መመደብ እንደሚችልና በቂ ዝግጅት ማድረጉ ሳያረጋግጥ፣

- የግል ባለሀብቶች በዘርፉ ቢሰማሩ በሀገሪቱ የኢኮኖሚ ደህንነት ላይ ሊያስከትል የሚችለው ተጽኖ በጥናት ሳይረጋገጥ፣
- ሽያጭ ሲፈጸም መብቱ ላላቸው አካላት ብቻ መሆኑን የሚረጋገጥበት ስርዓት ሳይዘረጋ፣
- የሽያጭ የአፈጻጸም መመሪያ ሳይዘጋጅ፣
- በዘርፉ የተሰማሩ በህግ የተቋቋሙ መንግስታዊ የልማት ድርጅቶች(የኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ስራ ድርጅት እና የኢትዮጵያ አየር መንገድ) እያሉ በቀረጥ ነጻ ንግድ ስራ ላይ ለሚሰማሩ ግለሰቦች በዘርፉ እንዲሰማሩ የሚያስችል ፈቃድ ለመስጠት አዋጁ (67/1989) ላይ ያልተመለከተ ዘርፍ በመሆኑ ለሚመለከተው ፈቃድ ሰጪ አካል (ገቢዎች ሚኒስቴር) በጻፈው ደብዳቤ "በቀረጥ ነጻ ንግድ ላይ የተሰማራው መንግስታዊ የልማት ድርጅትን (የኢትዮጵያ ቱሪስት ንግድ ስራ ድርጅት) ለማቋቋም የወጣውን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 106/85 የቀረጥ ነጻ ንግድ በመንግስት በሞኖፖል ለመያዙ ወይም በግል እንዳይሰራ የሚከለክል የተጠቀሰ አንቀጽ የሌለ በመሆኑ፣
    - የአስመጭነት የውጭ ንግድ ሥራ ፈቃድ፣
    - ከክልል የንግድ ኢንዱስትሪና ቱሪዝም ቢሮ የችርቻሮ ንግድ ስራ ፈቃድ እስካለው እና
- በተለይም በዓለም አቀፍ የአየር ማረፊያ ተርሚናል ውስጥ የኢትዮጵያ ሲቪል አቬዬሽን ባለስልጣን ከመደበው የቀረጥ ነጻ መሸጫ መደብር ውስጥ ሱቅ ለማግኘት የቻለ የንግድ ሥራውን ለመሥራት የሚያስችል የንግድ ሥራ ፈቃድ መሆኑ ታውቆ በዚሁ መሠረት እንዲፈፀም" በሚል በደብዳቤ ቁጥር ድ-አ.000171/7780 በ05/07/95 ባስተላለፈው ትዕዛዝ እንጂ በህግ በሚመለከተው ህግ-አውጪ አካል ተገቢው ህግ ወጥቶ የተሰማሩ አለመሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

27. የቀድሞው የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚ/ር መ/ቤት ካስተላለፈው ትዕዛዝ ለመረዳት እንደቻልነው ማንኛውን ከላይ የተጠቀሱትን ሶስት መስፈርቶች ያሟላ ማንኛውም ዜጋ የእድሉ ተጠቃሚ እንደሚሆን ነበር፡፡ ነገር ግን በዘርፉ ለመሰማራት የሚያስችል የህግ መሰረት ባለመኖሩ እና ወጥ የሆነ ስርዓት ባለመዘርጋቱ እድሉን በአንድ አጋጣሚ ካገኙት ሶስት የግል ድርጅቶች(አልፋራጅ ኃ/የተ/የግ/ድርጅት፣ ካንትሪ ትሬዲንግ እና ኑር ሁሴን ያሲን) በቀር በዘርፉ ለመሰማራት የሚፈልጉ አካላት ሁሉ እኩል መብት አለመስጠቱ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ ስለሆነም አሰራሩ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ከቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ሥራ ላይ ለተሰማሩ የግል ድርጅቶች በውጭ ምንዛሪ ለመቀበል የሚያስችል ፈቃድ አሰጣጥና እድሳት ተግባራዊ ስለመደረጉ፣

28. በቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት በውጭ ምንዛሪ ለመቀበል የሚያስችል ፈቃድ ማውጣትና በወቅቱ ማደስ አለባቸው፡፡

29. የቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ ስራ ላይ የተሰማራው አልፋራጅ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በአዲስ አበባ ኤርፖርት ተርሚናል አንድ እና ሁለት ውስጥ ለሁለት ሱቆቹ በውጭ ምንዛሪ ለመገበያየት የሚያስችል ፈቃድ ሳይኖረው እየሰራ ሲሆን፣ ፈቃድ ሰጪና ተቆጣጣሪ አካላትም(የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን) መስሪያ ቤቶችም ቢሆኑ፣ ፈቃድ እንዳለው ሳያረጋግጡ ከ10 ዓመት በላይ እየሰራ እንደሚገኝ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ችለናል፡፡

30. ይህን አስመልክቶ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በቀረበው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact sheet) ላይ በተሰጠው አስተያየት “በአዲስ አበባ ኤርፖርት ተርሚናል ውስጥ የቀረጥ ነጻ ሱቅ ያላቸው ሶስቱም የግል ድርጅቶች ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ በውጭ ምንዛሪ ለመቀበል የሚያስችል ፈቃድ ያላቸው መሆኑን ማረጋገጡን” ገልጿል፡፡

31. ይሁን እንጂ ሶስቱም የግል ድርጅቶች በውጭ ምንዛሪ ለመቀበል የሚያስችል ፈቃድ እንዳላቸው የተገለጸ ቢሆንም፣ በኦዲቱ ወቅት ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ባቀረብነው መጠይቅና ባገኘነው ማስረጃ መሰረት አልፋራጅ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ለሁለት ሱቆች በውጭ ምንዛሪ ለመገበያየት የሚያስችል ፈቃድ እንደሌለው ያረጋገጥን ስለሆነ የተሰጠውን መልስ አልተቀበልነውም፡፡

32. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ሥራ ላይ ለተሰማሩ የግል ድርጅቶች በውጭ ምንዛሪ ለመቀበል የሚያስችል ፈቃድ ለመስጠት የግል ድርጅቶች እንዲሰማሩ የሚፈቅድ ህግ ባለመኖሩ መስጠት እንደማይችሉ በደብዳቤ ለግል ድርጅቱ (አልፋራጅ ኃ/የተ/የግ/ማህበር) ገልጸው የነበረ ቢሆንም፣ ከኢትዮጵያ ሲቪል አቪየሽን ባለስልጣን በተደጋጋሚ በተጻፈ ደብዳቤ መሰረት ከቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ ስራ ላይ ለመሰማራት የሚያስችል ፈቃድ ሳይኖራቸው በውጭ ምንዛሪ ለመቀበል የሚያስችል ፈቃዱ ሊሰጣቸው ችሏል፡፡

33. በኛ አስተያየት ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ደህንነት ለማስጠበቅ የሚያስችል የፋይናንስ ስርዓት እንዲኖር የሚያደርግ ጥናት ሳይጠናና የቁጥጥር ስርዓት ሳይዘረጋ ፈቃድ የተሰጠ መሆኑ ታውቋል፡፡ ባንኩ በውጭ ምንዛሪ ለመቀበል እና ለመጠቀም ያወጣው መመሪያ ቁጥር 21/2003 እ.አ.አ ፈቃድ የተሰጣቸው አካላት የሰበሰቡትን የውጭ ሀገር ገንዘብ በቀጣይ ሁለት የስራ ቀናት ውስጥ በአቅራቢያቸው በሚገኝ የምንዛሪ ቢሮ ወይም ባንክ በመሄድ

መመንዘር/ማስገባት እንዳለባቸው ግዴታ የጣለ ቢሆንም፣ በመመሪያው መሰረት እንደማይፈጸም በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህ በመሆኑም ሀገሪቱ ማግኘት የሚገባትን የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ሊያሳጣት የሚችልና ያልተገባ የውጭ ምንዛሪ ዝውውር(Money loundry) አሰራር እንዲኖር እድል ይፈጥራል፡፡

34. ጥቅምት 20/2002ዓ.ም. በአዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ ኤርፖርት አስተዳደር ከአ/አ ቦሌ አለም አቀፍ ኤርፖርት አስተዳደር፣ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ ከአዲስ አበባ ኤርፖርት ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፣ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ከኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት በመሆን በወጪ መንገደኞች አዳራሽ ያለውን ህገ - ወጥ የግብይት ስርዓት አስመልክቶ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በውጭ ምንዛሪ ለመቀበል የሚያስችል ፈቃድ ሳይኖራቸው ግብይት የሚፈጽሙ መሆኑ የተለየና ለችግሩም ዘላቂ መፍትሄ እንዲያገኝ የሚከተሉት ሶስት ነጥቦች፡-

- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ጉዳዩ የሚመለከተው መ/ቤት በመሆኑ፣ የቁጥጥር ስርዓት በመዘርጋት ፈቃድ ሳይኖራቸው በውጭ ምንዛሪ የሚቀበሉ ነጋዴዎች ላይ ቁጥጥር ማድረግ
- ሕጋዊ ፈቃድ ኖሯቸው የሚሰሩ ድርጅቶች ከሽያጭ የሚያገኙትን የውጭ ምንዛሪ እዛው በሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ ገቢ እንዲያደርጉ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለመደብሮቹ ትእዛዝ እንዲያስተላልፍ የሚል እና
- በመንገደኞች አዳራሽ ውስጥ አብዛኛው ግብይት የሚፈጸመው በትራንዚት መንገደኞች በመሆኑ ከግብይት የሚገኘውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ በቀላሉ ለመቆጣጠርና ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ገቢ ለማሳደግ እንዲቻል በወጪ መንገደኞች አዳራሽ ውስጥ የሚገኙትን ሁሉንም የመሸጫ መደብሮች ወደ ቀረጥና ታክስ ነጻ አገልግሎት መስጫ እንዲቀየሩ

የተገለጸ ሲሆን፣ እድሉን በአንድ አጋጣሚ ካገኙት ሶስት የግል ድርጅቶች(አልፋራጅ ኃ/የተ/የግ/ድርጅት፣ ካንትሪ ትሬዲንግ እና ኑር ሁሴን ያሲን) በቀር በዘርፉ ለመሰማራት የሚፈልጉ አካላትን ያለማሳተፉና በዘርፉ የተሰማሩትም ቢሆኑ ለመሰማራት የሚያስችል የህግ መሰረት የሌላቸው መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

35. በወጪ መንገደኞች አዳራሽ በሁለቱም ተርሚናል ውስጥ ሁለት አይነት ንግድ ሲኖር ይኸውም ከቀረጥና ታክስ ነጻ እና ቀረጥና ታክስ ተከፍሎባቸው የሚሸጡ ዕቃዎች ንግድ ነው፡፡ በዚሁ አዳራሽ ተገቢ ያልሆነ(ህገ-ወጥ)ግብይት መኖሩ ስለታመነበት ባለድርሻ አካላት የሆኑት (የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን) ችግሩን ለመቅረፍ ተገቢው የግብይይት ስርዓት እንዲዘረጋ ጥናት

ቢጠናም፣ በቅንጅት ተገቢው የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አልተደረገም፡፡ በዚሁ አዳራሽ ከቀረጥና ታክስ ነጻ ያልሆኑ አካላትን በተመለከተ ከኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት ጋር የኪራይ ውል ሲፈጽሙ በሀገሪቱ ገንዘብ ለመገበያየት ሲሆን፣ ከብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ሳይኖራቸው በውጭ ምንዛሪ የሚገበያዩ እንደሆነ ለመረዳት ችለናል፡፡ በተጨማሪም ኤርፖርት ውስጥ በግለሰቦች የውጭ ሀገር ገንዘቦች ግዢ እና ሽያጭ እንደሚፈጸም በተለያየ ጊዜ በአዲስ አበባ ኤርፖርት ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ካጠናው ጥናት ለመረዳት ከመቻላችንም በላይ ከመስሪያ ቤታችን ለስራው ወጪ ባደረግነው ገንዘብ አንድ የአሜሪካን ዶላር በ23 የኢትዮጵያ ብር በመዘርዘር ለማረጋገጥ ችለናል፡፡

በቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ድርጅቶች የግል የዕቃ ማከማቻ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ አሰጣጥና እድሳትን በተመለከተ፤

36. የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት የግል ዕቃ ማከማቻ የጉምሩክ መጋዘን ለማቋቋም ከሚፈቀድላቸው አካላት ውስጥ ሰውና ጭነት የሚያጓጉዙ የአለም አቀፍ የአየር መንገድ ድርጅቶች እና እቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነጻ ለመሸጥ የተቋቋሙ አካላት ሲሆኑ የግል ዕቃ ማከማቻ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ ማውጣት ይኖርባቸዋል፡፡

37. ነገር ግን፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የጉምሩክ አዋጅ የሚመለከተው ሆኖ ሳለ፣ ከቀረጥና ታክስ ነጻ ዕቃዎችን በማስገባት በአየር ላይ (በበረራ ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉ እና ለሽያጭ የሚቀርቡ ዕቃዎች) የሚያከማችበት ቦንድድ መጋዘን የጉምሩክ ፈቃድ አለማውጣቱ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ የኢትዮጵያ አየር መንገድ (በበረራ ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉ እና ለሽያጭ የሚቀርቡ ዕቃዎችን) ማከማቻ መጋዘኖች ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ስዕል አንድ፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ መጋዘኖችን የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ

38. ስለሁኔታው ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በቀረበው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact sheet) ላይ በሰጠው አስተያየት "በበረራ ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉ ከቀረጥ ነጻ የሚያስገቧቸው እቃዎች የሚከማቹበትን መጋዘን ፈቃድ እንዲያወጣ ተደጋጋሚ ማሳሰቢያ እየተሰጠና ክትትል እየተደረገበት በሂደት ላይ መሆኑን" ገልጸዋል፡፡

39. ይሁን እንጂ የኦዲት ሥራው እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ማሳሰቢያ የተሰጠበት ደብዳቤ እና ክትትል ስለመደረጉ የሚገልጽ ማስረጃ አልቀረበም፡፡

የግል ዕቃ ማከማቻ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ ለግል የቀረጥ ነጻ ድርጅቶች ስለመሰጠቱ፡-

40. ከቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ስራ ላይ ለተሰማሩ የግል ድርጅቶች የግል ዕቃ ማከማቻ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ለቁጥጥርና ክትትል አመቺ መሆኑ ሳይረጋገጥ ፈቃድ ተሰጥቶ ተገኝቷል፡፡

41. የሶስቱም (አልፋራጅ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፣ ካንትሪ ትሬዲነግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፣ ኑር ሁሴን ያሲን ኃ/የተ/የግ/ማህበር) የግል የቀረጥ ነጻ ድርጅቶች ለረዥም ዓመታት የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘናቸው ከተማ የነበረ ሲሆን፣ እቃዎችም ከመጋዘን በመውጣት ህጋዊ ንግድ ላይ ተጽኖ የሚያሳድር በመሆኑ በ10 ቀናት ውስጥ ወደ ኤርፖርት ክልል እንዲገባ በቁጥር 50/4/1 ሐምሌ 05/2002 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ መወሰኑ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

42. ለግል ድርጅቶቹ መጋዘናቸው ከተማ ውስጥ በመሆኑ ለቁጥጥር አመቺ አለመሆኑ እየታወቀ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ እንዴት ሊሰጣቸው እንደቻለ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ (Fact Sheet) ተጠይቀው ሲመልሱ " ከ2002 ዓ.ም. ጀምሮ እስከነመጋዘናቸው በአዲስ አበባ ኤርፖርት ክልል ውስጥ እንዲገቡ ተደርገው በቅርበት ቁጥጥር ለማድረግ ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ" ተገልጿል፡፡

43. በኛ አስተያየት ባለስልጣኑ መስሪያ ቤት በአሁን ወቅት መጋዘኖቹ ወደ ኤርፖርት ክልል መግባታቸውን እና ቁጥጥር ለማድረግ ጥረት እየተደረገ እንደሆነ የገለጸ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት ለግል ድርጅቶቹ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ የተሰጠበት ሁኔታ ሲታይ፡-

   - መጋዘኖቹ ያሉበት አካባቢ ለቁጥጥር አመቺ መሆኑ ሳይረጋገጥ፣
   - ለክትተትልና ለቁጥጥር ተገቢው የሰው ሀይል ሳይመደብ፣
   - ለተመደቡ ሰዎች ምን እንደሚሰሩ የሚገልጽ የስራ መዘርዝር ሳይዘጋጅ እና
   - እንዴት እንደሚሰሩ የሚገልጽ ማኑዋል አለመዘጋጀቱ

   ለግል ድርጅቶቹ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ለክትትልና ቁጥጥር አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች ያልተለዩ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም መጋዘኖቻቸውም ወደ ኤርፖርት ክልል እንዲገቡ ሲወሰን፣ የተዘጋጁ መጋዘኖች ባለመኖራቸው እራሳቸው ኮንቴነር አዘጋጅተው

ዕቃዎቻቸውን እንዲያከማቹ በመደረጉ በሙቀት ለብልሽት የተዳረጉ መሆኑን በቦታው በመገኘት ለማየት ችለናል፡፡ የግል ድርጅቶቹ ዕቃዎቻቸውን የሚያከማቹበትን ኮንቴነር የሚያሳይ ምስል ከዚህ በታች ተመልክቷል፡፡

ስዕል ሁለት፡- የግል ድርጅቶቹ ዕቃ የሚያከማቹበትን ኮንቴነር የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ

44. በሌላም በኩል፣ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት እየተገነባ ያለው መጋዘን ባለበት ሁኔታ ከተጠናቀቀ በመንገድ ዳር ስለሚገኝ እና አጥር የሌለው በመሆኑ ለቁጥጥር የማያመች እንደሆነ በኦዲቱ ወቅት ተዟዙረን ከተመለከትነው ለመረዳት ችለናል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ በመገንባት ላይ የሚገኘው የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘንን ይመልከቱ፡፡

ስዕል ሶስት፡- በአሁን ሰዓት በመገንባት ላይ ያለው የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን

የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን እድሳትን በተመለከተ፡-

45. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ስለጉምሩክ መጋዘን የስራ ፈቃድ አሰጣጥን ለመወሰን በወጣው ደንብ ቁጥር 24/1990፡ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ በየበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ከሐምሌ 1 እስከ 30 ባለው ጊዜ ውስጥ ተገቢው ክፍያ ተፈጽሞ መታደስ እንዳለበት እና በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ፈቃድ ያላሳደሰ ከነሐሴ 1 እስከ ነሐሴ 30 ባለው ጊዜ የማደሻውን 100% ቅጣት በመክፈል ማሳደስ አለበት፡፡

46. ነገር ግን በአሁን ወቅት ሦስቱ የግል ድርጅቶች (አልፋራጅ ኃ/የተ/የግ ማህበር ፣ካንተሪ ትሬዲነግ ኃ/የተ/የግ ማህበር እና ኑር ሁሴን ያሲን ኃ/የተ/የግ ማህበር) ከነሐሴ 2002 ዓ.ም. ጀምሮ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃዳቸውን ሳያድሱ እየሰሩ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

47. ይህን አስመልክቶ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ተጠይቆ በሰጠው መልስ፣ የቀረጥ ነጻ ፈቃድ ያላቸው የግል ድርጅቶች የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘናቸው በከተማ ውስጥ የነበረ መሆኑ የአሰራር ክፍተት እንደሚፈጥር ታምኖበት፣ በኤርፖርት ክልል ውስጥ በጊዜያዊነት ዕቃ ማስቀመጫ እንዲዘጋጅላቸው በማድረግ እንዲገቡ መደረጉንና ይህም የተደረገው ከችግሩ አሳሳቢነት አንጻር ታይቶ እንጂ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ማሟላት ያለበትን አሟልቶ የተሰራ ባለመሆኑ፣ በጊዜያዊ ችግሩ ምክንያት ለጊዜው የመጋዘኑን ፈቃድ ማደስ አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡

48. በኛ አስተያየት ችግሩ ሊከሰት የቻለው ቀደም ብለን እንደገለጽነው ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት በቂ ዝግጅት ባለመደረጉ እና ተገቢው ጥናት ባለመጠናቱ ወቅታዊ ሁኔታዎችን በመከተል የቦንድድ መጋዘን ፈቃድ በመሰጠቱ ሲሆን፣ በዚህ ምክንያት መሰብሰብ የሚገባው የመንግስት ገቢ እንዳይሰበሰብ እና በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የገቡ ዕቃዎች በኮንቴነር መጋዘኑ ውስጥ በሙቀት ለብልሽት መዳረጉ እና እየተገነባ ያለው የመጋዘን ኮንስትራክሽን ስራ ገና መቼ እንደሚጠናቀቅ እርግጠኛ ባልሆነበት ሁኔታ ለችግሩ ጊዜያዊ መፍትሄ ለመስጠት የማያስችል መሆኑን ለመረዳት ችለናል፡፡

የቀረጥና ታክስ ነፃ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን የፈቃድ አሰጣጥ በመመሪያ መሠረት ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

49. የቀረጥ ነፃ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ ለመስጠት የጉምሩክ መጋዘን አስተዳደር የአፈጻጸም መመሪያው ላይ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት መሆን አለበት፡፡

50. ስለጉምሩክ መጋዘን አስተዳደር የአፈጻጸም መመሪያ ላይ ዓለም አቀፍ የአየር መንገዶች፣ እቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነጻ እንዲሸጡ የተፈቀደላቸው ድርጅቶችና ሌሎች ባለስልጣኑ ፈቃድ በሚሰጣቸው መሰረት የሚቋቋሙ የግል የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘኖች ካሉት አራት ደረጃዎች አራተኛ ደረጃ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን እንደሚሆን ተገልጿል፡፡ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን አራት ደረጃ ያለው ሲሆን እያንዳንዱ ደረጃ ሊያሟላ የሚገባው መስፈርትም የተለያየ ሲሆን፡-

- ለግል ድርጅቶቹ ፈቃድ የተሰጠበት መስፈርት አለመታወቁ፣
- በቀረጥ ነጻ ንግድ ስራ ላይ ለተሰማሩ አካላት ከመመሪያው ውጪ የተለያየ ደረጃ መሰጠቱ፣
- ለተለያየ የመጋዘን ፈቃድ ደረጃ አንድ አይነት ክፍያ የሚያስከፍል መሆኑ

በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

51. በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 4 እና 5 ላይ የጉምሩክ መጋዘን ማውጫ እና ማደሻ ክፍያ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ እንደሚወሰን የተገለጸ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት እየተሰራበት የነበረው በ1990ዓ.ም በወጣው ደንብ ቁጥር 24/1990 ላለፉት 15 ዓመታት ሳይሻሻል ለመጋዘን ፈቃድ ማውጫ የሚከፈለው ብር 1,250.00 እና ፈቃድ ለማደሻ ብር 500.00 መሆኑ ታውቋል፡፡

52. ስለሁኔታው ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በቀረበው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ (Fact sheet) ላይ በተሰጠው አስተያየት ለወደፊቱ ጥናት በማድረግ የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ ጥረት እንደሚያደርጉ እና አሁን በወጣው አዋጅ መሰረት እየሰሩ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

53. ይሁን እንጂ የመጋዘን ፈቃድ ማውጫ እና ማደሻ ክፍያን ለመወሰን እንዲያስችል ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ተጠንቶ የቀረበ ረቂቅ ደንብ ስለመኖሩ ተጠይቆ ማስረጃው አልቀረበልንም፡፡

54. ይህ መሆኑም መንግስት ለድርጅቶቹ ለሚሰጠው አገልግሎት (ፈቃድ መስጠት፣ ማደስ፣ ዕቃዎቹ ወደ መጋዘን በሚገቡበት ወቅት እና በመጋዘን ውስጥ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣ የዕቃ ፍተሻ ማድረግ…) የሚያወጣውን ወጪ የማይሸፍን መሆኑ እና ለተለያየ የቦንድድ መጋዘን ደረጃ አንድ አይነት ክፍያ እንዲከፈል እድል እንዲፈጥር አድርጓል፡፡

ወደ መጋዘን በገቡ እቃዎች ላይ ስርቆት የተፈጸመ ከሆነ የመጋዘን ፈቃድ እስከ መሰረዝ መድረሱን በተመለከተ

55. የጉምሩክ መጋዘን የስራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ ደንብ ቁጥር 24/1990 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ-ረ መሰረት በጥንቃቄ ጉድለት በእቃዎች ላይ ጉዳት ማድረስ፣ የጉምሩክ ፎርማሊቲ ያልተፈጸመባቸው ዕቃዎች ወደ ባለስልጣኑ መጋዘን በወቅቱ አለማስተላለፍና ሪፖርት አለማድረግ እንዲሁም በሌሎች ተመሳሳይ ምክንያት ለባለስልጠኑ ሹሞች ቀና አገልግሎት አለመስጠት፣ ወይም እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎች ድርጊቶችን መፈጸሙ ሲረጋገጥ ማስጠንቀቂያ የሚያሰጣቸውና ፍቃድ የሚሰረዝባቸው በደንቡ መሰረት ተፈጻሚ መደረግ አለበት፡፡

56. ነገር ግን የኢትዮጵያ አየር መንገድ በተደጋጋሚ ከላይ የተገለጹትን ድንጋጌዎች ሲጥስ ምንም አይነት ማስጠንቀቂያ አለመሰጠቱን እና እርምጃ አለመወሰዱን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

57. ይህን አስመልክቶ የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ለቀረበለት ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ(Fact Sheet) ላይ በሰጠው መልስ፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ካርጎ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጣ በተለያዩ ጊዜያቶች ማሳሰቢያ የተሰጠው መሆኑን፣ ውይይት የተደረገበት እና አሰራሩን እንዲያሻሽል ድጋፍ ሲደረግለት እንደቆየ ገልጸዋል፡፡

58. ይሁን እንጂ በተደጋጋሚ ለአየር መንገዱ ማስገንዘቢያ የተሰጠበት ማስረጃ፣ ከአየር መንገዱ ጋር የተደረገውን ውይይት የሚያሳይ ቃለ ጉባኤም ሆነ የተሰጠውን ድጋፍ የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበልንም፡፡ ይህ ባለመሆኑም በመጋዘኑ ውስጥ የሚፈጸው ያልተገባ ተግባር (በጥንቃቄ ጉድለት በእቃዎች ላይ ጉዳት የሚደርስ መሆኑ ለምሳሌ፡- በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወደ ሀገር የገቡ ዕቃዎች ወደ መጋዘን ሳይገቡ በፀሀይና በዝናብ መበላሸታቸው፣ በአያያዝና በአቀማመጥ ምክንያት የዕቃዎች መሰበር ወይም መያዣቸው በመጨራመታቸው ለሽያጭ እንዳይቀርቡ የተደረጉ መሆኑ …)በኦዲቱ ታይተዋል፡፡ ከዚህ በታች በአቀማመጥ ችግር በዝናብ ምክንያት የተጎዱ ዕቃዎችን የሚያሳይ ስዕል ይመልከቱ፡፡

ስዕል አራት፡- በአቀማመጥ እና በዝናብ ምክንያት የተጎዱ ዕቃዎችን የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ

በመጋዘን ውስጥ ስርቆት በሚፈጸምበት ወቅት እርምጃ ስለመወሰዱ፡-

59. የጉምሩክ መጋዘን የስራ ፈቃድ የሚሰጥበትን ሁኔታ ለመወሰን በወጣ ደንብ ቁጥር 24/1990 መሰረት ወደ መጋዘን በገቡ እቃዎች ላይ ስርቆት የተፈጸመ ከሆነ የመጋዘን ፈቃድ መሰረዝ አለበት፡፡

60. የኢትዮጵያ አየር መንገድ የሚያጓጉዘውን ዕቃ የሚያከማችበት መጋዘን ፈቃድ ያለው ሲሆን ዕቃዎች ላይ በተደጋጋሚ ስርቆት ሲፈጸም በደንቡ መሰረት የሚያሰርዝ ሆኖ ሳለ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ አለመሰጠቱ እና በመመሪያው መሰረት ቅጣት አለመፈጸሙ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

61. ለምን በደንቡ መሰረት እንዳልተፈጸመ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት ለቀረበለት ነባሪያዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጠው መልስ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ካርጎ በሀገሪቱ በአየር ለሚገቡ ዕቃዎች ብቸኛ አለም አቀፍ ካርጎ ተርሚናል ወደብ በመሆኑ ፍቃዱን መሰረዙ በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያስከትለውን ችግር ግምት ውስጥ በማስገባት አሰራሩን ለማሻሻል ትኩረት በመስጠት ሲከታተል መቆየቱ ተገልጿል፡፡

62. ይሁን እንጂ በደንቡ መሰረት የቦንድድ መጋዘን ፈቃድ የሚያሰርዝ ሆኖ ሳለ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ባለመሰጠቱ እና በመመሪያው መሰረት እርምጃ ባለመወሰዱ የሚፈጸመው ስርቆት እየተባባሰ ለመምጣቱ አስተዋጾ ከማድረጉም በላይ ተጠያቂነት እንዳይጠናከር እና ሀገሪቱ ልታገኝ የሚገባትን የውጭ ምንዛሪ እንዳታገኝ ሊያደርግ የሚያስችል በመሆኑ ተገቢው እርምጃ አለመወሰዱን አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

፪. ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሚፈጸምባቸው መሆኑ በተመለከተ

ከቀረጥና ታክስ ነፃ ዕቃዎች ወደ ቀረጥ ነፃ ሱቅ ከመግባተቸው በፊት የዕቃዎቹ ዝርዝር መረጃ በጉምሩክ መያዙን በተመለከተ

63. ከቀረጥና ታክስ ነፃ ዕቃዎች ወደ ቀረጥ ነፃ ሱቅ ከመግባታቸው በፊት የዕቃዎቹ ዝርዝር መረጃ (ዓይነትና ብዛት)ተጠናቅሮ በቀረጥ ነጻ መደብሮቹ እና በጉምሩክ መያዝ አለበት፡፡

64. አሰራሩ በኦዲቱ ሲታይ፣ ከቀረጥና ታክስ ነፃ ዕቃዎች ወደ ቀረጥ ነፃ ሱቅ ከመግባታቸው በፊት የዕቃዎቹ ዝርዝር መረጃ (ዓይነትና ብዛት) በጉምሩክ ተጠናቅሮ አለመያዙ፣ የእቃው መጠን ወደ አሲኩዳ ሲስተም(ጉምሩክ የሚጠቀምበት የኮምፒዩተር ፕሮግራም) ለማስገባት ከተወሰኑ ዕቃዎች በቀር ሲስተሙ ስለማይጠይቅ የዕቃዎቹ ዝርዝር መረጃ (ዓይነትና ብዛት) ወደ ሲስተም ካለመግባቱም በላይ መረጃው በሌላ መንገድ(በመዝገብ፣ በኮምፒዩተር...) የማይያዝ መሆኑ ታውቋል፡፡ እኛ እንደተረዳነው ለዚህም ዋነው ምክንያት ፈቃድ በተሰጠበት ወቅት በክፍሉ የተመደቡ ሰራተኞች የዕቃዎቹን መረጃ አለመያዛቸውን እና ምን መስራት እንዳለባቸው የሚገልጽ የስራ መዘርዝር(Job Description) አለመኖሩ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

65. ይህን አስመልክቶ ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት አሲኩዳ ሶፍር ዌር(software) የተሰራው በኢትዮጵያ ባለሙያዎች ሳይሆን በUN (united nation) እርዳታ በአለም አቀፍ ባለሙያዎች ስለሆነ ያንን ማስተካከል እንደማይቻል እና በቀረጥ ነጻ ንግድ ስራ ላይ ለተሰማሩ አካላት ፈቃድ ሲሰጥ የቀረጥ ነጻ ሱቆችን ለመምራት የሚያስችል መሰረታዊ የስራ ሂደት ጥናት ተከናውኖ ማንዋል በማዘጋጀት በቦታው ላይ የሚመደቡ ሰራተኞች እንዴት እንደሚሰሩ የሚገልጽ ሰነድ መቅረቡ ተገልጿል፡፡

66. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በቀረጥ ነጻ ንግድ ስራ ላይ ለተሰማሩ አካላት ፈቃድ ሲሰጥ(1994 ዓ.ም.) የተጠና ጥናት፣ ስራው ላይ ለተመደቡ ሰራተኞች የተዘጋጅቶ የተሰጠ የስራ መዘርዝር (Job description) እና በወቅቱ የተከናወኑ ተግባራትን የሚያሳይ ማስረጃ ሊቀርብ አልቻለም፡፡ ሆኖም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ስራውን በሚሰራው ቡድን በስራ መደቡ ላይ ለተመደቡ ሰራተኞች ተነሳሽነት የተዘጋጀ የስራ መዘርዝር ቀርቦልናል፡፡ ቡድኑ በራሱ ተነሳሽነት

ማዘጋጀቱን ብናደንቅም ከመርህ አንጻር ነጻ አካል ተጨምሮበት ወይም ተከልሶ እንዲጸድቅ አለመደረጉ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

67. በተጨማሪም በመስከረም 2000 ዓ.ም. የተጠናው (BPR) ጥናትም (ወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ንዑስ የሥራ ሂደት እና የቀረጥ ነፃ ሱቆች ፈቃድ አሰራር ንዑስ የስራ ሂደት) ላይ የተመለከተው እና የቡድን ስምምነት ላይ የተገለጹትም ተግባራት ቢሆን ከተወሰኑት በስተቀር እየተከናወነ አለመሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ችለናል፡፡ ለምሳሌ፡- የጉምሩክ ድርሻ የሽያጭ ደረሰኞች /Cash Sales Attachment/ በቅደም ተከተላቸው ተከታትሎ በማሰባሰብ ማረጋገጥና ለቡድን መሪው ማቅረብ፣ የመንገደኞች ዝርዝር በመረከብ ለባለመብቶች ብቻ መሸጡን ማረጋገጥ፣ የተከናወነው ሽያጭ ትክክለኝነት፣ በተወሰነ ጊዜ ቆጠራ ማከናወን እና ሌሎችም… ይገኙበታል፡፡

68. በኛ አስተያየት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መስሪያ ቤት ተገቢውን ጥናት አለማጥናቱ አገሪቱ ከዘርፉ ልታገኝ የሚገባትን ጥቅም ከማስቀረቱም በላይ የተከናወኑ ተግባራትን በሪፖርት ላለማቅረብ እና ተገቢው ክትትል እና ቁጥጥር በአግባቡ ለማከናወን እንዳይቻል እድል ፈጥራል፡፡

ከቀረጥና ታክስ ነጻ ወደ ሀገር የገቡ ዕቃዎች መረጃ በተመለከተ

69. ከቀረጥና ታክስ ነፃ ዕቃዎች ወደ ቀረጥ ነፃ ሱቅ ከመግባታቸው በፊት የዕቃዎቹ ዝርዝር መረጃ በጉምሩክ መያዝ አለበት፡፡

70. ከቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት ዕቃዎችን ወደ ሀገር በሚያስገቡበት ጊዜ መረጃው የS መለያ ቁጥር ተሰጥቶት ወደ ASYCUDA(Automated System for Customs Data Analysis) ሲስተም ሲመዘገብ አስር የተለያየ ዕቃ በአንድ ጊዜ አንድ ላይ ከመጣ ከአስሩ በአንዱ ከፍተኛ የታሪፍ መጠን ባለው የታሪፍ ኮድ ላይ የሚመደብ መሆኑ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

71. ለዚህ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መስሪያ ቤት ለቀረበለት ነባራዊ ሁኔታ(Fact Sheet) ሲመልሱ የቀረጥና ታክስ ልዩነት ባያመጣም መረጃ ላይ ልዩነት የሚፈጥር ስለሆነ በቀጣይ ሊስተካከል የሚገባው እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

72. ይህ መሆኑ በባለስልጣን መ/ቤቱ ለሚመለከተው አካል የሚቀርበው ሪፖርት ተአማኒነት የጎደለው፣ ትክክለኛ ያልሆነ፣ የመረጃውን ተጠቃሚ የሚያሳስት፣ እንዲሁም ለሚመደቡ ተቆጣጣሪዎች ስራቸውን ለማቅለል ወደ ሲስተም የገባውን መረጃ በመጠቀም የሚያከናውኑትን የክትትልና የቁጥጥር ስራ የማያቀል በመሆኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ወደ ጉምሩክ መጋዘን የሚገባ ዕቃ የሚመዘገብበት ስርዓት ስለመኖሩ፡-

73. የጉምሩክ መጋዘን አስተዳደር የአፈጻጸም መመሪያ 40/2002 ገጽ 6 ወደ ጉምሩክ መጋዘን የሚገባ ዕቃ የሚመዘገብበት መዝገብ እና ኮምፒተር የሚከተሉትን ዝርዝር የያዘ መሆን እንዳለበት ያሳያል፡፡ የመዝገብ ገጽ እና መለያ ቁጥር፣ የዕቃውን ባለቤትና ወኪል ስም፣ ዲክላራሲዮን ቁጥር ወይም የአየር ማጓጓዣ ሰነድ፣ ወደ መጋዘን ገቢ የሆነው ጠቅላላ የጥቅል ብዛት እና የመጠቅለያው ዓይነት፣ የዕቃዎቹ ስያሜ ከጥቅል ብዛታቸው ጭምር፣ ዕቃው ወደ መጋዘን የገባበትና ከመጋዘን የወጣበት ቀን እና የአስረካቢ እና የተረካቢ ስምና ፊርማ መኖር አለበት፡፡

74. ነገር ግን በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መስሪያ ቤት የቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት የኢትዮጵያ አየር መንገድን ጨምሮ የሚፈለጉ ማስረጃዎች በሚፈለገው ደረጃ ፈቃድ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ አለመያዙ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

75. ለዚህ ኦዲት ተደራጊው መስሪያ ቤት ሲመልስ የግል መጋዘኖቹ ኤርሳይድ ከገቡበት ጊዜ ጀምሮ ቆጠራ ተደርጎ የዕቃው አይነትና መጋዘን የገባበት ቀን፣ ከመጋዘን የወጣበት ቀን እና ቀሪውን የሚያሳይ መረጃ በኮምፒተር በኤክሴል አፕልኬሽን ሶፍት ዌር እንደሚመዘገብ ገልጸዋል፡፡

76. በኛ አስተያየት ኦዲት ተደራጊው መስሪያ ቤት ለግል ድርጅቶቹ ፈቃድ ከተሰጠበት ከ1994 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 2002ዓ.ም.(ወደ ኤርፖርት ክልል) እስከ ገቡበት ድረስ በመጋዘን የገቡትን እና የሚቀሩትን የዕቃዎች መጠን የሚያሳይ መረጃ አለመያዙ የተሟላ መረጃ ለማግኘት ካለማስቻሉም በላይ በሚያከናውነው በክትትልና ቁጥጥር ስራ ላይ አሉታዊ ተጽኖ ያሳድራል፡፡

በፍተሻ ወቅት የተገኘ ልዩነት ስለመተላለፉ፡-

77. በአየር ማረፊያ ውስጥ ዕቃው ወደ ቀረጥ ነፃ ሱቅ ሲገባ ሰነድ ተቀብሎ መፈተሽ፣ የፍተሻ ውጤት ከዲክላራሲዮን አባሪ ሰነዶች ጋር ማመሳከር፣ የፍተሻ ውጤቱ ልዩነት ካለው ለህግ ማስከበር ማስተላለፍ፣ የፍተሻ ውጤቱ ልዩነት ከሌለው መተማመኛ በመፈራረም አንድ ቅጅ ለቀረጥ ነፃ ሱቅ በመስጠት ፋይል መደረግ አለበት፡፡

78. ይሁን እንጂ በተለያየ ጊዜ እቃዎች ሲፈተሹ ከዲክላራሲዮን አባሪ ሰነዶች ጋር ሲመሳከር ልዩነት ሲኖር (ሲጎድል) በሰነዱ ጀርባ ላይ የመጻፍ እንጂ ለየትኛውም አካል (ለህግ ማስከበርም ሆነ ለስራ ሂደቱ) ሪፖርት የማይደረግ መሆኑ፣ ችግሩም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ የመጣ ሲሆን ከ10 ዓመት በላይ የችግሩን መንስኤ በመለየት ለመፍታት የተሰራ ስራ አለመኖሩ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ችለናል፡፡

79. ለዚህ ባለስልጣን መ/ቤቱ በሰጠው መልስ፣ በፍተሻ ወቅት ልዩነት ሲገኝ በአስተዳደራዊ ውሳኔ መሰረት የሚፈጸም ሲሆን የልዩነቱን መንስኤንም ለማወቅ ጥረት እንደሚደረግ ተገልጿል፡፡

80. ኦዲት ተደራጊው መስሪያ ቤት ይህን ይበል እንጂ በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ እንደተቻለው መስሪያ ቤቱ ከ10 ዓመት በፊት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በተለያየ ምክንያት ከቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት ዕቃዎችን ከውጭ አስገብተው በሚፈተሹበት ወቅት ከሰነዱ ጋር ሲመሳከር አንሶ ሲገኝ የችግሩን መንስኤ በመለየት አለመፍታቱ፣ ሪፖርት አለመያዙ እና መፍትሔ አለመሰጠቱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

81. በተቆጣጣሪው መስሪያ ቤት የጉዳዩን አሳሳቢነት በመረዳት ለሚመለከተው ሁሉ ሪፖርት አለማድረጉ እና መፍትሄ አለመፈለጉ ችግሩም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ እንዲመጣ ከፍተኛ አስተዋጾ አድርጓል፡፡ ይህ በመሆኑም ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የወጣበት ዕቃ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልበት ባልተገባ መንገድ(በስርቆት) ወደ ገበያ በማስገባት የገበያ አለመረጋጋት ይፈጥራል፣ መንግስት ከንግዱ ማግኘት የነበረበትን ታክስ ከማሳጣቱም በላይ ከዕቃዎች ሽያጭ መሰብሰብ የነበረበትን የውጭ ምንዛሪ እንዳይገባ በር ይከፍታል፡፡

፫. ለቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ስራ መመሪያና የአሠራር ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ

በቀረጥ ነፃ ሱቆች ውስጥ ጊዜ ያለፈባቸውና በሚጓጓዙበት ወቅት ጉዳት ለደረሰባቸው ዕቃዎች ለማስወገድ የአፈፃፀም መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ስለመደረጉ

82. በቀረጥ ነፃ ሱቆች ውስጥ ጊዜ ያለፈባቸው፣ ረጅም ጊዜ ያስቆጠሩ እና በሚጓጓዙበት ወቅት መጠነኛ ጉዳት የደረሰባቸውን ዕቃዎች በሽያጭም ሆነ በሌላ መንገድ ለማስወገድ የሚያስችል የአፈፃፀም መመሪያ እና ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

83. በዘርፉ የተሰማሩ ድርጅቶች ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገቧቸውን ጊዜ ያለፈባቸው በሚጓጓዙበት ወቅት መጠነኛ ጉዳት ለደረሰባቸው እና ረዥም አመታትን ላስቆጠሩ ዕቃዎች የአፈፃፀም መመሪያ እና ለማስወገድ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች ሳይወገዱ ረዥም ጊዜ ሱቅ/መጋዘን ውስጥ እንደሚገኙ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከቀረጥና ታክስ ነጻ ያስገባቸውን ዕቃዎች ሲያስወግድ ተቆጣጣሪው አካል (የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት) ሳያውቀው ከአየር መንገዱ የበላይ ኃላፊ ማረጋገጫ ከተገኘ በኋላ ከአየር መንገዱ ሴኩሪቲ፣ ከውስጥ ኦዲት፣ እና ከቤዝ ሰርቪስ ተወካዮች ሲገኙ የሚወገድ መሆኑን ለመረዳት ችለናል፡፡ ከዚህ በመቀጠል በሚጓጓዙበት ወቅት መጠነኛ ጉዳት የደረሰባቸው ዕቃዎችን የሚያሳይ ምስል ተመልክቷል፡፡

ስዕል 5፡- በከፊል የተጎዱ ዕቃዎችን የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ

84. ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ለቀረበለት የኦዲቱ ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ በሰጠው መልስ ለቀረጥ ነጻ ሱቆች ብቻ የሚያገለግል የተበላሹ እቃዎችን ለማስወገድ ተብሎ የወጣ መመሪያ ባይኖርም፣ ነገር ግን በአጠቃላይ እቃዎችን ለማስወገድ በወጣው መመሪያ መሰረት እየተፈጸመ እንደሚገኝ እና ጉዳት ለደረሰባቸው እቃዎች የካሳ ክፍያ በአጓጓዥ ድርጅት አማካይነት የሚከፈል ስለሆነ የአፈጻጸም መመሪያ የማያስፈልገው እንደሆነ ተገልጿል፡፡

85. በኛ አስተያየት ኦዲት ተደራጊው መስሪያ ቤት መመሪያ አለ ቢልም፣ በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ያሉ ዕቃዎች አወጋገድ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 56/2003 ላይ በሚጓጓዙበት ወቅት መጠነኛ ጉዳት ስለደረሰባቸው እና ከቀረጥና ታክስ ነጻ ገብተው ረጅም አመታትን ያስቆጠሩ ዕቃዎች ማስወገድን በተመለከተ በመመሪያው ላይ የተጠቀሰ ካለመሆኑም በላይ በሚጓጓዙበት ወቅት መጠነኛ ጉዳት ለደረሰባቸው ዕቃዎች በኢንሹራንስ ስለሚሸፈን ዕቃዎቹን ለማስወገድ የሚያስችል ተገቢው የአፈፃፀም መመሪያ እና የአሰራር ሥርዓት ሊዘረጋለት አይገባም የሚል እምነት የለንም፡፡ በሚጓጓዙበት ወቅት መጠነኛ ጉዳት የደረሰባቸው ዕቃዎች ወጪ በኢንሹራንስ የሚሸፈን ቢሆንም ዕቃውን ኢንሹራንሶች ቀረጥና ታክስ ከፍለው ለማውጣት ፍላጎት አይኖራቸውም፡፡

86. የአፈፃፀም መመሪያ እና የአሰራር ሥርዓት ባለመኖር በቀረጥ ነፃ ድርጅቶች ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የወጣባቸው ረጅም አመታትን ያስቆጠሩ ያልተሸጡ ዕቃዎች መኖራቸው (ለዘመናት ተከማችተው መገኘታቸው) ዕቃዎቹ ተሸጠው ለሀገሪቱ ተጨማሪ የውጭ ምንዛሪ ገቢ ለማግኘት ካለመቻሉም በላይ ጥቅም ላይ እንዳይውሉ(እንዲበላሹ) ሊያደርግ ይችላል፡፡

87. በኢትዮጵያ አየር መንገድ ከቀረጥና ታክስ ነጻ ገብተው በተለያየ ምክንያት ዕቃዎችን ሲያስወግድ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት (የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና ሌሎቹም) በመመሪያው መሰረት ዕቃው መወገዱን እና ከአካባቢ ብክለት አንጻር ማስወገጃ ቦታ የተዘጋጀ ስላለ አካባቢን በማይበክል መንገድ መወገዱን ጭምር ሊያረጋግጥ ስለሚገባ አሰራሩ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የቀረጥና ታክስ ነጻ ዕቃዎች ሽያጭ አፈጻጸምን በተመለከተ

88. በቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ ላይ ለተሰማሩ አካላት የሽያጭ አፈጻጸም ሥርዓት እና የተዘጋጀ የሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡

89. በቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ ላይ ለተሰማሩ አካላት የሽያጭ አፈጻጸም ሥርዓት እና የተዘጋጀ የሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት አለመዘጋጀቱ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

90. ይህን አስመልክቶ ኦዲት ተደራጊው መስሪያ ቤት ሲመልስ የተለየ የሽያጭ መመሪያ ባይዘጋጅም ሽያጭ መከናወን እንዳለበት እና ለእነማን አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው በአሰራር ማንዋሉ ላይ የተገለጸ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

91. ይሁን እንጂ በኛ አስተያየት ኦዲት ተደራጊው መስሪያ ቤት ያዘጋጀው ማንዋል የመደባቸው ተቆጣጣሪዎች ማከናወን ያለባቸውን ተግባር እንዴት እንደሚያከናውኑ ለመረዳት የሚያስችል እንጂ በዘርፉ ለተሰማሩ አካላት የሽያጭ አፈጻጸም ሥርዓት እና የሽያጭ አፈፃፀም መመሪያ ሆኖ አልተገኘም፡፡

92. ይህ መሆኑም በዘርፉ ለተሰማሩ አካላት እንዴት፣ ለማን፣ ምን ሲሟላ መሸጥ እንደሚችሉ፣ የኮታ መጠን(ካስፈለገ)፣ በውጭ ሀገር ገንዘብ መቀበል እንዳለባቸው፣ ሪፖርት ማቅረብ እንዳለባቸው፣ ወጥ የሆነ የሪፖርት አቀራረብ፣ ሪፖርቱ ምን መያዝ እንዳለበት፣ እና መያዝ ያለባቸውን መረጃዎች (በሶፍትም ሆነ በሀርድ ኮፒ) እንዲያዘጋጁ ካለማድረጉም በላይ ተገቢውን ቁጥጥር ለማድረግ አያስችልም፡፡

፱.የቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ አሰራርን በተመለከተ

93. ለቀረጥ ነፃ ሱቆችና መብት ላላቸው ተጠቃሚዎች ቀረጥ ነፃ አሰራርን በተመለከተ የራሳቸውን ኃላፊነትና ግዴታ በአግባቡ እንዲወጡ ለማስቻል የግንዛቤ ማስጨበጫ በየጊዜው መሰጠት አለበት፡፡

94. ከቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ላይ የተሰማሩ አካላትና መብት ላላቸው ተጠቃሚዎች ስለ ቀረጥ ነፃ አሰራር ኃላፊነትና ግዴታቸውን እንዲያውቁት አለመደረጉ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

95. ይህን አስመልክቶ ኦዲት ተደራጊ መስሪያ ቤት ጉዳዩ የሚመለከታቸው የስራ ሂደት ሲመልሱ በዘርፉ ለተሰማሩ ድርጅቶች ስለተግባርና ኃላፊነታቸው በየጊዜው ለማስገንዘብ ጥረት እየተደረገ እንደሆነ እና የመብቱ ተጠቃሚዎችን በተመለከተ በቀላሉ ስለማይገኙ ግንዛቤ ለመፍጠር አመቺ አለመሆኑን የገለጹ ሲሆን፣ በተጨማሪም በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ(Fact Sheet) ሲመልሱ ማንዋሎችን በማዘጋጀት እንዲያውቁት መደረጉን እና ድርጅቶቹ በሚሰሩት ስራ ጥንቃቄ በማድረግ መብቱ ከሚፈቅድለት ውጪ ሽያጭ እንዳያከናውኑ ግንዛቤ መፈጠሩን ገልጸዋል፡፡

96. ይሁን እንጂ የግንዛቤ ማስጨበጫ ለመስጠት የተለያዩ ቀላል መንገዶች(ለምሳሌ በቀረጥ ነጻ ሱቆቹ ውስጥ በመለጠፍ፣ በራሪ ጽሁፎችን በማደል...) እያሉ አመቺ አይደለም መባሉን ያልተቀበልነው መሆኑና፣ ጉምሩክ ማንዋል ያዘጋጀው ለሚመድባቸው ተቆጣጣሪዎች ለመቆጣጠር እንዲችሉ ምን ሲሚላ ሽያጭ እንደሚፈጸም የተዘጋጀ እንጂ ግንዛቤ ማስጨበጫ ለመስጠት የተዘጋጀ እንዳልሆነ ለመረዳት ችለናል፡፡

97. የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ በተለያየ ጊዜ ባለመሰጠቱም እና ግዴታቸውን በማይወጡት ላይ የተጣለ ቅጣት የሌለ በመሆኑ በዘርፉ የተሰማሩ ድርጅቶች መብት ለሌላቸው አካላት የሚሸጡ መሆኑ፣ መብቱ ያላቸው አካላትም ቢሆኑ መብቱ ለሌላቸው አካላት የሚገዙ መሆኑ እና ባለመብት ያልሆኑ አካላትም በተለያየ ጊዜ በባለመብቶች እንዲያስገዙ በር ከፍቷል፡፡

፲.የቀረጥ ነፃ ዕቃዎች ሽያጭ ሂደትና የጉምሩክ ክትትልና ቁጥጥር ውጤታማ መሆኑን ማጣራት

ከቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች የሽያጭ ሪፖርት ጉምሩክ በመቀበል ትክክለኝነቱ መረጋገጥ እና ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ

98. የቀረጥ ነፃ ሱቆች የሽያጭ ሂደትን ተከትለው የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ መደረግ እና የሚቀርበው ሽያጭ ሪፖርት ትክክለኝነቱ በየጊዜው መረጋገጥ አለበት፡፡

99. የግል ድርጅቶቹ ፈቃድ ከማግኘታቸው በፊት የወጡ ህጎችን በመከለስ በሀገሪቱ የኢኮኖሚ ደህንነት ለማስጠበቅ የሚያስችል የፋይናንስ ሥርዓት በመዘርጋት የሚኖረውን ተጽዕኖ በመዳሰስ ጉዳዩ ይመለከተናል ያሉ ፈቃድ ሰጪ አካላት(የቀድሞ ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ገቢዎች ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ) ተገቢው ጥናት በማጥናትና የቀረጥ ነጻ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች የሚያከናውኑትን የሽያጭ ሂደት ተከትሎ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት አለመዘርጋቱን ለማወቅ ችለናል፡፡

100. በአጠቃላይ በመንግስትም ሆነ በግል የቀረጥ ነጻ መደብሮች እና የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከቀረጥና ታክስ ነጻ በማስገባት በአየር ላይ ከቀረጥና ታክስ ነጻ የሚፈጽም ሽያጭ ሂደቱን ተከትሎ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ አለመደረጉ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

101. ይህን አስመልክቶ ኦዲት ተደራጊው መስሪያ ቤት ለቀረበለት ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ሲመልስ፣ በቀረጥ ነጻ ንግድ ስራ ላይ ለተሰማሩ አካላት ፈቃድ በሚሰጥበት ወቅት ሀገሪቱ በአለም አቀፍ ደረጃ የተፈራረመቻቸውን ስምምነቶች መሰረት በማድረግ ከሚገቡ እና ከሚወጡ አለም አቀፍ መንገደኞች የሚገኘውን የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ በተጨማሪም ኤርፖርቱ የሚሰጠውን ፋሲሊቲ ለማጠናከር ያግዛል ከሚል ታሳቢ ሲሆን ቁጥጥሩን በተመለከተ ኤርፖርት ክልል ውስጥ በመሆኑ በሌሎች ተጓዳኝ መስሪያ ቤቶች ድጋፍ ጭምር ቁጥጥር እንደሚደረግበት ታሳቢ በማድረግ ነበር፡፡ እንዲሁም የወሩ የሽያጭ ሪፖርት የሚሰበሰብ ሲሆን በሲስተም የተደገፈ ባለመሆኑ ትክክለኝነቱ የማይረጋገጥ መሆኑን ተገልጿል፡፡ ሌላው ሰራተኞችን አብቃቅቶ ከማሰራት አንጻር ለተወሰኑ ጊዜያቶች ሽያጭ በሚከናወንባቸው ሱቆች ተቆጣጣሪ ሳይመደብ የቆየ ቢሆንም በጥናት በተገኘው ማረጋገጫ ክፍተቶች በመታየታቸው አሁን ሰራተኛ እንዲመደብ መደረጉን ገልጸዋል፡፡

102. በኛ አስተያየት ለድርጅቶቹ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት፡-

- በሀገሪቱ የወጡ ህጎች የግል ድርጅቶች በዘርፉ እንዲሰማሩ የሚፈቅድ መሆኑ፣
- በዘርፉ የግል ድርጅቶቹ ቢሰማሩ በሀገሪቱ የኢኮኖሚ ደህንነት እና የኢኮኖሚ መረጋጋት ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ተጽዕኖ መለየት፣
- በሀገሪቱ ተገቢው የፋይናንስ ስርዓት እንዲኖር ከማድረግ አንጻር መዳሰስ፣
- መንግስት ቀረጥና ታክሱን በመተው ተቆጣጣሪ በመመደብ ለሚያወጣው ወጪ ሊሸፍን የሚችል አሰራር መዘርጋቱን ማረጋገጥ፣

- ተገቢውን የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት በመዘርጋት የገበያ አለመረጋጋት አለመፈጠሩና ህጋዊ ንግዱን ሊያዳክም አለመቻሉን ማረጋገጥ፣
- ከዕቃዎች ሽያጭ መግባት የነበረበትን የውጭ ምንዛሪ በአግባቡ እንዳይገባ እድል አለመፍጠሩ፣ የውጪ ምንዛሪ በህገ-ወጥ መንገድ የሚዘረዘርበት ስርዓት አለመኖሩ፣
- የሀገር ልማትና እድገት በተገቢው መንገድና ፍትሀዊ በሆነ መንገድ እንዳይኖር በር የማይከፍት መሆኑ፣
- በህገ-ወጥ መንገድ የተገኘን ገንዘብ ህጋዊ ማድረግን /Money laundry እንዳይኖር የሚያደርግ ስርዓት መኖሩን እና
- ሀገሪቱ ከዘርፉ ልታገኝ የሚገባትን ጥቅም እንድታገኝ መመቻቸቱ

ታስቦበት ተቆጣጣሪ እና ፈቃድ ሰጪ አካላት (የቀድሞው ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ) ተገቢውን የክትትልና የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት ቅድሚያ ሊሰጡት ይገባ ነበር፡፡ ነገር ግን ተገቢው የቁጥጥና የክትትል ስርዓት ሳይዘረጋ ኤርፖርት ክልል ውስጥ በመሆኑ በሌሎች ተጓዳኝ መስሪያ ቤቶች ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል የጋራ ስምምነት ላይ ሳይደረስ ቁጥጥር እንደሚደረግ ታስቦ መወሰዱ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

103. በሀገሪቱ የወጡ ህጎች (አዋጆችና ደንቦች) በአግባቡ ሳይዳሰሱ የግል ድርጅቶቹ በዘርፉ እንዲሰማሩ ሲፈቀድ ሀገሪቱ ከዘርፉ ልታገኝ የሚገባትን ጥቅም እንድታገኝ የሚያደርግ ስርዓት ባለመዘርጋቱ ማግኘት ያለባትን ጠቀሜታ እንዳታገኝ ሊያደርግ ይችላል፡፡

የቀረጥ ነጻ ዕቃዎች ሽያጭ ትክክነኝነቱ ስለመረጋገጡ፡-

104. በቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት የየቀኑ የዕቃ ሽያጭ ደረሰኝ ቅጅ ለጉምሩክ መድረስና የሚቀርበው ሪፖርትም ትክክለኝነት በክፍሉ እና በታክስ ኦዲት ድንገተኛ ኦዲት በማድረግ(surprise Audit) መረጋገጥ አለበት፡፡

105. የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከቀረጥና ታክስ ነጻ በአየር ላይ ለሚፈጸም ሽያጭ ማስረጃ (የሽያጭ ደረሰኝ) ለተገልጋዮቹ የማይሰጥ እንደሆነና የሽያጭ ሪፖርት ለጉምሩክ እንደማያቀርብ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

106. ለዚህ ኦዲት ተደራጊው መስሪያ ቤት ለቀረበለት ነባራዊ ሁኔታ ሲመልስ፣ አየር መንገድ (በበረራ ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉና ለሽያጭ የሚቀርቡ ዕቃዎች) ላይ ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ ተገልጿል፡፡

ሽያጭ ለባለመብቶች ብቻ ስለመፈጸሙ

107. የቀረጥ ነጻ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት ከቀረጥና ታክስ ነፃ ያስገቧቸውን ዕቃዎች ለዓለም አቀፍ መንገደኞች ብቻ የሚሸጡ መሆኑን የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ከአጓጓዥ ድርጅቶች ስም ዝርዝር በመቀበል ማረጋገጥ አለበት፡፡

108. በኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና በኢትዮጵያ አየር መንገድ መካከል ሚያዝያ 1995 ዓ.ም. የተፈጸመ የመግባቢያ ሰነድ እና የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ንውስ የሥራ ሂደት እና ቀረጥ ነፃ ሱቆች ፈቃድ አሠራር ንዑስ የሥራ ሂደት (BPR) የጥናት ሰነድ ላይ ከአጓጓዥ ድርጅቶች የዓለም አቀፍ መንገደኞችን ስም ዝርዝር ተቀብሎ መረጃ መያዝ እንዳለበት ተገልጿል፡፡ ነገር ግን በአዲስ አበባ ቦሌ ኤርፖርት የሚገኙ የቀረጥ ነጻ ንግድ ላይ የተሰማሩ አካላት ከቀረጥና ታክስ ነፃ ያስገቧቸውን ዕቃዎች ለዓለም አቀፍ መንገደኞች ብቻ የሚሸጡ መሆኑን ከአጓጓዥ ድርጅቶች ስም ዝርዝር በመቀበል እንደማይረጋገጥ እና የሚፈለገው የቁጥጥር ስራ አለመሰራቱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

109. ይህን በተመለከተ ኦዲት ተደራጊው መስሪያ ቤት ለቀረበለት ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ሲመልስ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የሚያመጣውን የመንገደኞች ማኒፌስት ለመጠቀም የሚያስችል ሲስተም የተዘረጋ ባለመሆኑ ለወደፊቱ ይህንኑ አጠናክሮ መስራት አስፈላጊ መሆኑ እንደታመነበት ገልጸዋል፡፡

110. በኛ አስተያየት በአዲስ አበባ ቦሌ ኤርፖርት የቀረጥ ነጻ መደብሮች ከተከፈቱ ከ10 ዓመት በላይ የሆናቸው ሲሆን፣ ዕቃዎች ለዓለም አቀፍ መንገደኞች ብቻ የሚሸጡበትን ስርዓት በመዘርጋት፣ ከአጓጓዥ ድርጅቶች የመንገደኞች ስም ዝርዝር በመቀበል የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የማረጋገጥ መሆኑ እና የቁጥጥር ስራ አለመሰራቱ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት ወደ ሀገር ያስገቧቸው ዕቃዎችን የሚያከማቹበት መጋዘኖችና ሱቆች ውስጥ የገባ ዕቃ መረጃ መያዙን እና ክትትልና ቁጥጥርን በተመለከተ

111. የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገባቸው ዕቃዎች (ቦንድድ መጋዘን) በባለስልጣኑ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ አለበት፡፡

112. በቀድሞው በኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና በኢትዮጵያ አየር መንገድ መካከል ሚያዝያ 1995 ዓ.ም. የተፈጸመ የመግባቢያ ሰነድ ላይ "አየር መንገዱ በበረራ ወቅት ጥቅም ላይ የሚያውላቸውና ከቀረጥና ነጻ የሚሸጣቸው ዕቃዎች በጉምሩክ ቁጥጥር እየተደረገባቸው ወደ ተዘጋጀላቸው መጋዘን ይገባሉ፤መጋዘኑም በሁለት የተለያዩ ቁልፎች እንዲቆለፍ ተደርጎ

ሁለቱም መ/ቤቶች አንዳንድ ቁልፍ እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ አየር መንገዱ ከላይ የተመለከቱትን ዕቃዎች ወደ መጋዘኑ እንደገቡ ወዲያውኑ ዲክለር/ያሳውቃል/ ያደርጋል፡፡ አየር መንገድ በበረራ ወቅት ጥቅም ላይ ያዋላቸውንና ከቀረጥ ነፃ የሸጣቸውን ዕቃዎች በተመለከተ ለጉምሩክ በየወቅቱ መግለጫ ያቀርባል፡፡ በበረራ ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉና ከቀረጥ ነጻ የሚሸጡ ዕቃዎች ወደ በረራ እንዲገቡ በሚዘጋጁበት ወቅት ጉምሩክ በቦታው በመገኘት ቁጥጥር ያደርጋል፡፡ በበረራ ወቅት ጥቅም ላይ ያልዋሉት እና በቀረጥ ነፃ የልተሸጡት ዕቃዎች በጉምሩክ ቁጥጥር እየተደረገባቸው ወደ መጋዘን ይመለሳሉ፡፡" የሚሉ ጉዳዮች ላይ ስምምነት ያደረጉ ቢሆንም በአሁን ወቅት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገባቸው ዕቃዎች በባለስልጣኑ ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

113. ይህን አስመልክቶ ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሲመልስ፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከቀረጥና ታክስ ነጻ የሚያስገባቸውን ዕቃዎች በተመለከተ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ እንዲያወጣ በተደጋጋሚ ማሳሰቢያ እንደተሰጠው ተገልጿል፡፡

114. ሆኖም ይህ ለመደረጉ ተቆጣጣሪው መ/ቤት አየር መንገዱ ተገቢውን የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ እንዲያወጣ እና ተገቢውን የክትትልና ቁጥጥር ተግባር ለመፈጸም የሚያስችል ስራ መሰራቱን የሚያመለክት ማስረጃ አላቀረበም፡፡

115. ይህ የቁጥጥርና የክትትል ስራ ባለመከናወኑ በተለያየ መንገድ ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለባቸው በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚገቡ ዕቃዎች በቀላሉ እንዲወጡ ከማድረጉ ባሻገር ህጋዊውን ገበያ በማዛባት የገበያ አለመረጋጋት ሊፈጥር ይችላል፡፡

በቦንድድ መጋዘን እና በመደብሮች ላይ ቆጠራ ስለመደረጉ

116. በቀረጥ ነፃ ሱቅና መጋዘን ውስጥ ያሉ ዕቃዎች በሱቅ ወይም በመጋዘን ውስጥ በትክክል መኖራቸውን ቆጠራ በማከናወንና የቆጠራ ውጤቱንም ከመረጃ ጋር በማገናዘብ በመብለጥና በማነስ የተገኙ ዕቃዎች ካሉ በሪፖርት መሰረት ተጣርቶ እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

117. የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት በዘርፉ ከተሰማሩ አካላት በቀረጥ ነፃ መደብር እና መጋዘን ውስጥ ያሉ ዕቃዎች ቆጠራ የማይካሄድ መሆኑ፣ ወደ ቀረጥ ነፃ ሱቅ የገባ ዕቃ ለባለመብቶች ተሸጦ የቀረውን ዓይነትና መጠን የሚገልጽ መረጃ በጉምሩክ የማይያዝ መሆኑ፣ የዕቃውን ቆጠራ ውጤትን ከቀረበው ሪፖርት ጋር በማመሳከር ሪፖርት የማይዘጋጅ መሆኑ እና የቁጥጥርና የክትትል ስራ በጉምሩክ የማይሰራ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

118. ይህን አስመልክቶ ኦዲት ተደራጊው መስሪያ ቤት ለቀረበለት ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ሲመልስ በመጋዘን ላይ ቁጥጥር እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡

119. ይሁን እንጂ በዘርፉ የግል ድርጅቶቹ እንዲሰማሩ ሲፈቀድ የሚያዝ መረጃ ያልነበረ መሆኑ፣ በአሁን ወቅት በሱቆችም ሆነ በመጋዘኖች ላይ ቆጠራ የማይደረግ መሆኑ እና መጋዘናቸው ወደ ኤርፖርት ክልል እንዲገባ በተወሰነ ጊዜም ቢሆን ቆጠራ ይደረግ እንጂ የቆጠራው ውጤቱ (ባላንሱ) ለመነሻ እንዲሆን አለመያዙ ቁጥጥሩን የተሟላ አያደርገውም፡፡

120. በኛ አስተያየት ተገቢው ቁጥጥር ባለመደረጉ ምክንያት የተሸጠ እና ያልተሸጠ ዕቃ ካለመታወቁም በላይ ህጋዊውን ገበያ ሊያዛባ እና ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት ያለባትን ገቢ ሊያሳጣ ይችላል፡፡

ክፍል ሦስት

መደምደሚያ

የቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ሥራ ፈቃድ ፣ በውጭ ምንዛሪ መገበያየት የሚያስችል ፈቃድ እና የመጋዘን ፍቃድ አሰጣጥን በተመለከተ፡-

- በኦዲቱ ወቅት በቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ስራ ላይ ተሰማርተው በመስራት ላይ የሚገኙት የግል የቀረጥ ነጻ ድርጅቶች በቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ስራ ላይ ለመሰማራት የሚያስችል የህግ መሰረት እና ተገቢው የንግድ ሥራ ፈቃድ የላቸውም፡፡
- በኦዲቱ ወቅት የቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ ስራ ላይ የተሰማራው አልፋራጅ ኃ/የተ/የግ/ማህበር በአዲስ አበባ ኤርፖርት ተርሚናል አንድ እና ሁለት ውስጥ ካሉት ሶስት ሱቆች ለሁለቱ ሱቆቹ በውጭ ምንዛሪ ለመገበያየት የሚያስችል ፈቃድ የለውም፡፡
- የኢትዮጵያ አየር መንገድ የጉምሩክ አዋጅ የሚመለከተው ሆኖ ሳለ ከቀረጥና ታክስ ነጻ ዕቃዎችን በማስገባት በአየር ላይ (በበረራ ወቅት ጥቅም ላይ የሚውሉ እና ለሽያጭ የሚቀርቡ ዕቃዎች) የሚያከማችበት ቦንድድ መጋዘን የጉምሩክ ፈቃድ አላወጣም፡፡
- በአሁን ወቅት ሦስቱ የግል ድርጅቶች (አልፋራጅ ኃ/የተ/የግ ማህበር ፣ካንተሪ ትሬዲነግ ኃ/የተ/የግ ማህበር እና ኑር ሁሴን ያሲን ኃ/የተ/የግ ማህበር) ከነሐሴ 2002 ዓ.ም. ጀምሮ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃዳቸውን አላደሱም፡፡
- የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን አራት ደረጃ ያለው ሲሆን እያንዳንዱ ደረጃ ሊያሟላ የሚገባው በመመሪያው ላይ በተቀመጠው መስፈርትመስፈርት መሰረት ተግባራዊ አልተደረገም፡፡
- በኢትዮጵያ አየር መንገድ የሚያጓጉዛቸውን ወደ መጋዘን በገቡ እቃዎች ላይ ስርቆት እየተፈጸመ ማስጠንቀቂያ አልተሰጠም፣ ቅጣት አልተቀጣም እና ፈቃዱም አልተሰረዘም፡፡

ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሚፈጸምባቸው መሆኑ በተመለከተ

- ከቀረጥና ታክስ ነፃ ዕቃዎች ወደ ቀረጥ ነፃ ሱቅ ከመግባታቸው በፊት የዕቃዎቹ ዝርዝር መረጃ (ዓይነትና ብዛት)ተጠናቅሮ በሲስተምም ሆነ በመዝገብ በጉምሩክ አይያዝም፡፡
- ወደ ጉምሩክ መጋዘን የሚገባ ዕቃ የሚመዘገብበት መዝገብ እና ኮምፒዩተር ዲክላራሲዮን ቁጥር፣ የአየር ማጓጓዣ ሰነድ፣ ጥቅል ብዛታቸው፣ ዕቃው ወደ መጋዘን የገባበትና ከመጋዘን የወጣበት ቀን እና የአስረካቢና የተረካቢ ፊርማ በተሟላ መልኩ አይያዝም፡፡
- ከቀረጥና ታክስ ነፃ ዕቃዎች ወደ ቀረጥ ነፃ ሱቅ ከመግባታቸው በፊት የዕቃዎቹ ዝርዝር መረጃ (ዓይነትና ብዛት)ተጠናቅሮ በቀረጥ ነጻ መደብሮቹ እና በጉምሩክ አይያዝም፡፡

- ከቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት ዕቃዎችን ወደ ሀገር በሚያስገቡበት ጊዜ መረጃው የS መለያ ቁጥር ተሰጥቶት ወደ አሲኩዳ ሲስተም ሲገባ(ሲመዘገብ) የዕቃዎቹ ብዛት ሲስተሙ የማይጠይቅ መሆኑ እና አስር የተለያየ ዕቃ በአንድ ጊዜ አንድ ላይ ከመጣ ከአስሩ በአንዱ ከፍተኛ የታሪፍ መጠን ባለው የታሪፍ ኮድ ላይ ይመደባል፡፡
- ወደ ጉምሩክ መጋዘን የሚገባ ዕቃ የሚመዘገብበት መዝገብ እና ኮምፒዩተር ዲክላራሲዮን ቁጥር፣ የአየር ማጓጓዣ ሰነድ፣ ጥቅል ብዛታቸው፣ ዕቃው ወደ መጋዘን የገባበትና ከመጋዘን የወጣበት ቀን እና የአስረካቢና የተረካቢ ፊርማ በተጠነከረ መልኩ አይያዝም፡፡

ለቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ስራ መመሪያና የአሠራር ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ

- ከቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገቧቸው ዕቃዎች በሚጓጓዙበት ወቅት መጠነኛ ጉዳት ለደረሰባቸው እና ረዥም አመታትን ላስቆጠሩ ዕቃዎች የአፈፃፀም መመሪያ እና ለማስወገድ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ባለመደረጉ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎች ሳይወገዱ ረዥም ጊዜ መጋዘን ውስጥ ሳይሸጥ ይገኛል፡፡
- የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከቀረጥና ታክስ ነጻ ያስገባቸውን ዕቃዎች ተቆጣጣሪው መ/ቤት በሌለበት ያስወግዳል፡፡

የቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ አሰራርን በተመለከተ

- ለቀረጥ ነፃ ሱቆችና መብት ላላቸው ተጠቃሚዎች ቀረጥ ነፃ አሰራርን በተመለከተ የራሳቸውን ኃላፊነትና ግዴታ በአግባቡ እንዲወጡ ለማስቻል የግንዛቤ ማስጨበጫ በየአመቱ አይሰጥም፡፡

የቀረጥ ነፃ ዕቃዎች ሽያጭ ሂደትና የጉምሩክ ክትትልና ቁጥጥር ውጤታማ መሆኑን ማጣራት

- የቀረጥ ነፃ ሱቆች የሽያጭ ሂደትን ተከትለው የቁጥጥርና የክትትትል ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ መደረግ እና የሚቀርበው ሽያጭ ሪፖርት ትክክለኘነቱ አይረጋገጥም፡፡
- የቀረጥ ነጻ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት ከቀረጥና ታክስ ነፃ ያስገቧቸውን ዕቃዎች ለዓለም አቀፍ መንገደኞች ብቻ የሚሸጡ መሆኑን ከአጓጓዥ ድርጅቶች ስም ዝርዝር በመቀበል አይረጋገጥም፡፡
- የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገባቸው ዕቃዎች (ቦንድድ መጋዘን) በባለስልጣኑ ክትትልና ቁጥጥር አይደረግም፡፡

በአጠቃላይ የቀረጥ ነጻ ንግድ አሠራርና አፈጻጸም መመሪያ ካልተዘጋጀ፣ በመመሪያው መሠረት እየተሰራ ካልሆነ፣ ለቀረጥ ነጻ ድርጅቶች ከቀረጥና ታክስ ነጻ ለመነገድ የሚያስችል የንግድ ስራ ፈቃድ ከሌላቸው፣ በውጭ ምንዛሪ መቀበል የሚያስችል ፈቃድ ከሌላቸው፣ የቦንድድ መጋዘን ፈቃድ ከሚመለከታቸው ፈቃድ ሰጪ አካላት ከሌላቸው፣ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት የግል ድርጅቶች

የቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ ላይ ለመሰማራት የሚያስችል ህግ ከሌለ፣ የቀረጥ ነጻ ንግድ ድርጅቶች ከውጭ ዕቃ ሲያስገቡ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሚፈጸም ካልሆነ፣ የቀረጥ ነጻ ሱቆች ከቀረጥና ታክስ ነጻ ያስገቧቸውን ዕቃዎች ሽያጭ የሚያከናውኑበት መንገድ ግልጽና ተጠያቂነትን በሚያሰፍን መልኩ ካልሆነ፣ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ካልተዘረጋ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በባለመብቶች ዙሪያ መደበኛ የሆነ ቅንጅታዊ አሰራር ከሌለ እና የመረጃ ልውውጥ ሥርዓትና ግንኙነት ካልተዘረጋ ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት በሚገባት ጥቅም ላይ አሉታዊ ተጽኖ ስለሚያሳድር በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን የአሰራር ግድፈቶችና ድክመቶች ለማረም እንዲቻል የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ሀሳቦች

የቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ሥራ ፈቃድ ፣ በውጭ ምንዛሪ መገበያየት የሚያስችል ፈቃድ እና የመጋዘን ፍቃድ አሰጣጥን በተመለከተ፡-

- በቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ስራ ላይ ለመሰማራት የሚፈልጉ አካላት የህግ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ እና በዚሁ መሰረት ከቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ ሥራ ፈቃድ ማውጣትና በወቅቱ ሊያድሱ ይገባል፡፡
- በቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት በውጭ ምንዛሪ ለመቀበል የሚያስችል ፈቃድ ማውጣትና በወቅቱ ሊያድሱ ይገባል፡፡
- በቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ማናቸውም አካላት የግል ዕቃ ማከማቻ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ ሊያወጡ ይገባል፡፡
- በቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት የግል ዕቃ ማከማቻ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ (ከሀምሌ 1 እስከ 30) ሊያድሱ ይገባል፡፡
- የቀረጥ ነፃ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ ለመስጠት በመመሪያው ላይ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡
- ወደ መጋዘን በገቡ እቃዎች ላይ ስርቆት የተፈጸመ ከሆነ ፍቃድ የሚሰረዝባቸውና ማስጠንቀቂያ የሚያሰጣቸው በደንቡ መሰረት ተፈጻሚ ሊደረግ ይገባል፡፡

ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሚፈጸምባቸው መሆኑ በተመለከተ

- ከቀረጥና ታክስ ነፃ ዕቃዎች ወደ ቦንድድ መጋዘን እና ቀረጥ ነፃ ሱቅ ከመግባታቸው በፊት የዕቃዎቹ ዝርዝር መረጃ (ዓይነትና ብዛት)ተጠናቅሮ በቀረጥ ነጻ መደብሮቹ እና በጉምሩክ ሊያዝ ይገባል፡፡
- ወደ ጉምሩክ መጋዘን የሚገባ ዕቃ የሚመዘገብበት መዝገብ እና ኮምፒዩተር ዲክላራሲዮን ቁጥር፣ የአየር ማጓጓዣ ሰነድ፣ ጥቅል ብዛታቸው፣ ዕቃው ወደ መጋዘን የገባበትና ከመጋዘን የወጣበት ቀን እና የአስረካቢና የተረካቢ ፊርማ ሊኖር ይገባል፡፡

ለቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ስራ መመሪያና የአሠራር ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ

- በቀረጥ ነፃ ሱቆች ውስጥ ጊዜ ያለፈባቸውና በሚጓጓዙበት ወቅት ጉዳት ለደረሰባቸው ዕቃዎች በሽያጭም ሆነ በሌላ መንገድ ለማስወገድ የሚያስችል የአፈፃፀም መመሪያ እና ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

የቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ አሰራርን በተመለከተ

- ለቀረጥ ነፃ ሱቆችና መብት ላላቸው ተጠቃሚዎች ቀረጥ ነፃ አሰራርን በተመለከተ የራሳቸውን ኃላፊነትና ግዴታ በአግባቡ እንዲወጡ ለማስቻል የግንዛቤ ማስጨበጫ በየአመቱ ሊሰጥ ይገባል፡፡

የቀረጥ ነፃ ዕቃዎች ሽያጭ ሂደትና የጉምሩክ ክትትልና ቁጥጥር ውጤታማ መሆኑን ማጣራት

- የቀረጥ ነፃ ሱቆች የሽያጭ ሂደትን ተከትለው የቁጥጥርና የክትትትል ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ መደረግ እና የሚቀርበው ሽያጭ ሪፖርት ትክክለኝነቱ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
- በቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት የየቀኑ የዕቃ ሽያጭ ደረሰኝ ቅጅ ለጉምሩክ መድረስና የሚቀርበው ሪፖርትም ትክክለኝነት በክፍሉ እና የታክስ ኦዲት ድንገተኛ ኦዲት በማድረግ(surprise Audit) ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
- የቀረጥ ነጻ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ አካላት ከቀረጥና ታክስ ነፃ ያስገቧቸውን ዕቃዎች ለዓለም አቀፍ መንገደኞች ብቻ የሚሸጡ መሆኑን ከአጓጓዥ ድርጅቶች ስም ዝርዝር በመቀበል ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
- የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገባቸው ዕቃዎች (ቦንድድ መጋዘን) በባለስልጣኑ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት ለስራችን ቀና ትብብር ያደረጉልንን የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መስሪያ ቤት የስራ ኃላፊዎችና ሰራተኞች፣ በቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ የመንግስት እና የግል ድርጅት የስራ ኃላፊዎችና አካላትን፣ ለተባባሩን አካላት ሁሉ ላደረጉልን የሥራ ትብብር ከልብ እናመሰግናለን!

አባሪ 1

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት፡-የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

የኦዲት አካባቢ፡-የቀረጥ ነፃ ንግድ አሰራርና አፈጻጸም ብቃት ያለውና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ /Audit Issues/	የመመዘኛ መስፈርት /Evaluative Criteria/
1. የቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ሥራ እና የመጋዘን ፍቃድ አሰጣጥን በተመለከተ 1.1. የቀረጥ ነፃ ንግድ ሥራ ፈቃድ፣ በውጭ ምንዛሪ መቀበል የሚያስችል ፈቃድ እና የመጋዘን ፍቃድ አሰጣጥና እድሳት ወጥ በሆነ መልኩ ተግባራዊ መሆኑንና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ	1. በቀረጥ ነፃ ንግድ ለመሰማራት ለሚፈልጉ አካላት የንግድ ስራ፣ የጉምሩክ መጋዘን እና ከብሔራዊ ባንክ በውጭ ምንዛሪ መገበያየት እንዲችሉ የሚያስችል ፍቃድ ማግኘት አለባቸው፡፡
	2. ለቀረጥና ታክስ ነፃ ንግድ ፍቃድ አሰጣጥና እድሳት ወጥ የሆነ መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መሆን አለበት፡፡
	3. በቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ መሰማራት ለሚፈልጉ አካላት የንግድ ፈቃድ ለማደስ ከብሔራዊ ባንክ በውጭ ምንዛሪ መገበያየት እንዲችሉ የሚያስችል ፈቃድ ሲኖራቸውና በወቀቱ ሲያድሱ ብቻ መሆን አለበት፡፡
1.2. የቀረጥ ነፃ ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ አሰጣጥና እድሳት ወጥ በሆነ መልኩ ተግባራዊ መሆኑንና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ	4. በቀረጥ ነጻ ንግድ ላይ ለተሰማሩ አካላት ሁሉ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ መሰጠት አለበት፡፡
	5. የቀረጥ ነፃ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን ፈቃድ ለመስጠት በተቀመጠው መስፈርት መሰረት መሆን አለበት፡፡
	6. የቀረጥና ታክስ ነፃ የጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን የፈቃድ አሰጣጥ በመመሪያ መሠረት ተግባራዊ መሆን አለበት፡፡
	7. የቀረጥ ነፃ የጉምሩክ ቦንደድ መጋዘን የፈቃድ አሰጣጥና እድሳት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
	8. በቀረጥ ነፃ ንግድ ሥራ የተሰማሩ ባለሀብቶች የተሰጣቸውን የመጋዘን ፍቃድ በወቅቱ (ከሀምሌ 1 እስከ 30) ማደስ አለባቸው፡፡
	9. ወደ መጋዘን በገቡ እቃዎች ላይ ስርቆት የተፈጸመ ከሆነ የመጋዘን ፈቃድ ሊሰረዝ ይገባል፡፡
	10. ፍቃድ የሚሰረዝባቸውና ማስጠንቀቂያ የሚያሰጣቸው በደንቡ መሰረት ተፈጻሚ መደረግ አለበት፡፡
2. ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚገቡ ዕቃዎች	11. ከቀረጥና ታክስ ነፃ ዕቃዎች ወደ ቀረጥ ነፃ ሱቅ ከመግባታቸው በፊት የዕቃዎቹ ዝርዝር መረጃ (ዓይነትና ብዛት) ተጠናቅሮ በቀረጥ ነጻ

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ /Audit Issues/	የመመዘኛ መስፈርት /Evaluative Criteria/
የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት የሚፈጸምባቸው መሆኑ ማጣራት	መደብሮቹ እና በጉምሩክ መያዝ አለበት፡፡
	12. ወደ ጉምሩክ መጋዘን የሚገባ ዕቃ የሚመዘገብበት መዝገብ እና ኮምፒዩተር ዲክላራሲዮን ቁጥር፣ የአየር ማጓጓዣ ሰነድ፣ ጥቅል ብዛታቸው፣ ዕቃው ወደ መጋዘን የገባበትና ከመጋዘን የወጣበት ቀን እና የአስረካቢና የተረካቢ ፊርማ መኖር አለበት፡፡
	13. የፍተሻ ጥያቄ በሚቀርብበት ጊዜ አስፈላጊ ሰነዶችን ከቀረጥ ነፃ ሱቆች መቀበልና ከሰነዶች (የዕቃው ዴክለራሲዮን፣ የዕቃው ዝርዝር መግለጫ ፣ የዕቃው ኢንቮይስ ወዘተ) ጋር በማገናዘብ ዕቃ መፈተሽና መቆጠር አለበት፡፡
	14. በፍተሻ ወቅት በቆጠራ ውጤቱ መሠረት ልዩነት ከተገኘ ለህግ ማስከበር (ለኢንፎርስመን) መተላለፍ ይኖርበታል፡፡
	15. በቆጠራ ወቅት ልዩነት ካልተገኘ ከሱቁ ተወካይ ጋር መተማመኛ በመፈራረም አንድ ቅጅ ለሱቁ ተወካይ በመስጠት መተማመኛው ፋይል መደረግ አለበት፡፡
	16. በጭነት ወቅት የተጎዱና የቀረጥ ነፃ ዕቃዎችን በሽያጭም ሆነ በሌላ መንገድ ለማስወገድ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
3. የቀረጥ ነፃ ዕቃዎች ሽያጭ ሂደትና የጉምሩክ ክትትልና ቁጥጥር ውጤታማ መሆኑን ማጣራት	17. ከቀረጥ ነፃ ሱቆች የሽያጭ ሪፖርት በየወሩ ለጉምሩክ መድረስና ትክክለኝነቱም በክፍሉ፣ በታክስ ኦዲትና በድንገተኛ ኦዲት መረጋገጥ አለበት፡፡
	18. በቀረጥ ነፃ ሱቅና መጋዘን ያለውን ዕቃ በጉምሩክ በየሶስት ወሩ ቆጠራ በማካሄድ መተመመኛ መቀበል አለበት፡፡
	19. የዓለም አቀፍ መንገደኞችን ስም ዝርዝር ከአጓጓዥ ድርጅቶች በመቀበል መረጃ መያዝ አለበት፡፡
	20. የቀረጥ ነጻ ንግድ ድርጅቶች ከቀረጥ ነፃ የገቡ ዕቃዎች ለዓለም አቀፍ መንገደኛ ብቻ መሸጣቸውን፣ በተጠናቀረው መረጃ መሠረት በማገናዘብ ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
	21. ወደ ቀረጥ ነፃ ሱቅ የገባ ዕቃ ለባለመብቶች የተሸጠና የቀረ ዕቃ ዓይነትና መጠን የሚገልጽ መረጃ በየወሩ ጉምሩክ መያዝ አለበት፡፡
	22. የየቀኑ የቀረጥ ነጻ ንግድ ሱቆች የዕቃ ሽያጭ ደረሰኝ ቅጅ ለጉምሩክ መድረስ አለበት፡፡
	23. ያልተሸጡ ዕቃዎች በሱቁ ወይም በመጋዘን ውስጥ በትክክል መኖራቸውን በየሶስት ወሩ ቆጠራ በማከናወንና የቆጠራ ውጤቱንም ከመረጃ ጋር መገናዘብ አለበት፡፡
	24. በቆጠራ ወቅት በመብለጥና በማነስ የተገኙ ዕቃዎች ላይ በቀረበው ሪፖርት መሰረት ተጣርቶ እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ /Audit Issues/	የመመዘኛ መስፈርት /Evaluative Criteria/
	25. ለቀረጥ ነፃ ሱቆችና መብት ላላቸው ተጠቃሚዎች ስለ ቀረጥ ነፃ አሰራርን በተመለከተ የራሳቸውን ኃላፊነትና ግዴታ በአግባቡ እንዲወጡ ለማስቻል የግንዛቤ ማስጨበጫ በየአመቱ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡
	26. በቀረጥ ነፃ ሱቆች ውስጥ ጊዜ ያለፈባቸውና በሚጓጓዙበት ወቅት ጉዳት ለደረሰባቸው ዕቃዎች የአፈፃፀም መመሪያ መዘጋጀትና ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
	27. የሥራ ጊዜያቸውን ጨርሰው የተሰናበቱ የቀረጥ ነፃ ባለመብቶች የስራ ጊዜያቸውን አጠናቀው ሲሰናበቱና አዲስ ለሚመጡ ስርዓት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
	28. የቀረጥ ነፃ ሱቆች የሽያጭ ሂደትን ተከትለው የቁጥጥርና የክትትትል ሥርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
	29. የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከቀረጥና ታክስ ነፃ የሚያስገባቸው ዕቃዎች (ቦንድድ መጋዘን) በባለስልጣኑ ቁጥጥርና ክትትል መደረግ አለበት፡፡
	30. የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከቀረጥና ታክስ ነጻ በማስገባት በአየር ላይ የሚፈጽመውን ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሽያጭ ላይ ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
	31. የቀረጥ ነጻ ሱቅ አሰራርና ክትትል፣ የባለመብቶች ደረጃና የአገልግሎት መጠን መመሪያ መዘጋጀትና ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
	32. የቀረጥ ነፃ ንግድን በተመለከተ በየጊዜው የሚወጡ ህጎች፣ መመሪያዎችና ደንቦችን ወጥ በሆነ መልኩና በጽሑፍ ተዘጋጅቶ በዘርፉ ለተሰማሩ ሁሉ እንዲደርሳቸው መደረግ አለበት፡፡
	33. በቀረጥ ነፃ ንግድን በተመለከተ ከሚመለከተው አካል ጋር ቅንጅታዊ አሰራርና የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት መኖር አለበት፡፡ የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ተዘርግተው ተግባራዊ መደረግ አለበት፡፡
	34. በቀረጥ ነፃ ሱቆች ላይ ሕገወጥ ንግድን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል ድንገተኛ ፍተሻ መካሄድ አለበት፡፡

አባሪ-2

በኦዲቱ የታዩ መ/ቤቶች እና ድርጅቶች ዝርዝር

- በአልፋራጅ ወጪ መንገደኞች ተርሚናል አንድ በሚገኝ አንድ ሱቅ እና ተርሚናል ሁለት በሚገኙ ሁለት ሱቆች በድምሩ ሶስት ሱቆች፣
- በካንትሪ ትሬዲንግ ተርሚናል አንድ ወጪ መንገደኞች በሚገኝ አንድ ሱቅ፣
- በኑር ሁሴን ወጪ ተርሚናል አንድ መንገደኞች በሚገኝ አንድ ሱቅ፣
- በኢትዮጵያ ቱሪስትና ንግድ ስራ ድርጅት ሱቆች (በገቢ መንገደኞች ተርሚናል አንድ በሚገኝ አንድ ሱቅ፣ በወጪ መንገደኞች በሚገኝ አንድ ሱቅ፣ በቪ.አይ.ፒ በሚገኝ አንድ ሱቅ በተርሚናል ሁለት ወጪ መንገደኞች በሚገኝ አንድ ሱቅ እና በገቢ መንገደኞች በሚገኝ አንድ ሱቅ ከኤርፖርት ውጪ ፤በሃያ ሁለት ዋናው ቀረጥ ነጻ ሱቅ፣ በሂልተን፣ በግዮን ሆቴሎች እና በኢ.ሲ.ኤ የሚገኙ የቀረጥ ነጻ ሱቆች) እና
- በኢትዮጵያ አየር መንገድ ነው፡፡
- በአጠቃላይ በኦዲቱ የተዳሰሱት አልፋራጅ ሦስት፤ ካንትሪ ትሬዲንግ አንድ፤ ኑር ሁሴን አንድ፤ የኢትዮጵያ ቱሪስትና ንግድ ስራ ድርጅት ዘጠኝ ሱቆች በድምሩ አስራ አራት (14) ሱቆች እና የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሲሆን ከቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ አሠራር ጋር ግንኙነት ያላቸው የተለያዩ ባለድርሻ አካላት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ንግድ ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ምልከታ የተደረገባቸው አካላት ናቸው፡፡

አባሪ-3

ቃለ መጠይቅና መጠይቅ የቀረበላቸው አካላት

ቃለ መጠይቅ የቀረበላቸው አካላት

1. ለደንበኞች አገልግሎት አ/አ ኤርፖርት ጉምሩክ
2. ለህግ ማስከበር የስራ ሂደት
3. ለመንገስት የተሰጡ መብቶች የስራ ሂደት
4. የኢትዮጵያ አየር መንገድ
5. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
6. ለቱሪስት ንግድ ስራ ድርጅት
7. ለአልፋራጅ ኃ.የተ.የግ.መህበር
8. ለካንትሪ ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.መህበር
9. ለኑር ሁሴን ኃ.የተ.የግ.መህበር

መጠይቅ የቀረበላቸው

1. በአ/አ ኤርፖርት ገቢዎችና ጉምሩክ ጽ/ቤት ለደንበኞች አገልግሎት የስራ ሂደት
2. በአ/አ ኤርፖርት ገቢዎችና ጉምሩክ ጽ/ቤት ለህግ ማስከበር የስራ ሂደት መብቶች
3. በአ/አ ኤርፖርት ገቢዎችና ጉምሩክ ጽ/ቤት ለመንገደኞች ጓዝ የስራ ሂደት
4. አ/አ ኤርፖርት ገቢዎችና ጉምሩክ ጽ/ቤት በደንበኞች አገልግሎት የሥራ ሂደት ለመንግስት የተሰጡ መብቶች ቡድን
5. አ/አ ኤርፖርት ገቢዎችና ጉምሩክ ጽ/ቤት በመንግስት የተሰጡ መብቶች ቡድን ለ22 የኢ.ቱ.ን.ድ ላይ ለተመደቡ የጉምሩክ ተቆጣጣሪዎች
6. አ/አ ኤርፖርት ገቢዎችና ጉምሩክ ጽ/ቤት በደንበኞች አገልግሎት የሥራ ሂደት ለአጠቃላይ ቅሬታ ቡድን
7. አ/አ ኤርፖርት ገቢዎችና ጉምሩክ ጽ/ቤት በመንገደኞች ጓዝ ለኤር ሳይድ ቡድን አስተባባሪ
8. አ/አ ኤርፖርት ገቢዎችና ጉምሩክ ጽ/ቤት በጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም ሥራ ሂደት ለወጪ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም ንዑስ የስራ ሂደት ቡድን አስተባባሪ
9. በአ/አ የወጪና ሌሎች ዕቃዎች ማስተናገጃ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ለመንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተሰጡ መብቶች አስፈፃሚ ቡድን አስተባባሪ
10. በኢትዮጵያ አየር መንገድ ለፋይናንስና ኮርፖርት ቫይስ ፕሬዜዳንት
11. በኢትዮጵያ አየር መንገድ ለኬቴርንግ ዳይሬክተር
12. በኢትዮጵያ አየር መንገድ ለምግብና መጠጥ ቁጥጥር
13. በኢትዮጵያ አየር መንገድ ለምግብ ደህንነትና ጥራት ቁጥጥር
14. በኢትዮጵያ አየር መንገድ ለሰኩሪቲ መምሪያ
15. በኢትዮጵያ አየር መንገድ ለከተሪነግ ዳይሬክተር ኢንፍላይት ሰርቪስን
16. በኢትዮጵያ አየር መንገድ ለመጋዘን እና ዕቃ ግዥ ማናጀር
17. በኢትዮጵያ አየር መንገድ ለኳሊቲ ኮንትሮል ማናጄር
18. በኢትዮጵያ ኤርፖርት ድርጅት ለገበያ ማጎልበት ዳይሬክቶርት
19. በኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት ለደንበኞች ጉዳይ አገልግሎት
20. በኢትዮጵያ ኤርፖርት ድርጅት ለአ/አ ቦሌ አለም አቀፍ ኤርፖርት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር
21. ቤሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት የጥበቃ ዋና መመሪያ ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ፍተሻና ቁጥጥር ክፍል
22. በቤሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት የጥበቃ ዋና መመሪያ ለካርጎና ከተሪንግ ቁጥጥር ዋና ክፍል
23. በንግድ ሚኒስቴር ለንግድና ምዝገባ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር
24. በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለዲፕሎማቲክ መብት ጥበቃና ከለላ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር
25. ለአቃቂ ክፍለ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት
26. ለቦሌ ክፍለ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት
27. ለአራዳ ክፍለ ከተማ ለንግድና ኢንዱስትሪ ልማት
28. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
29. ለቱሪስት ንግድ ስራ ድርጅት
30. ለአልፋራጅ ኃ.የተ.የግ.መህበር
31. ለካንትሪ ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.መህበር
32. ለኑር ሁሴን ኃ.የተ.የግ.መህበር

አባሪ 4

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ድርጅታዊ መዋቅር



አባሪ 5

ባለስልጣኑ በጀት እቅድ አፈፃፀም

ተ.ቁ	የበጀት ዓመት		ደመወዝና ስራ መስኬጃ	ካፒታል	በፒስካኘ	ጠቅላላ ድምር ለባለስልጣኑ የተመደበው
1.	2002	እቅድ	339,828,714	8,492,514	25,777,360.00	374,098,588.00
		ክንውን	334,629,219	7,151,584	21,819,059.95	363,599,862.95
		ክንውን በመቶኛ	**98.47**	**84.21**	**84.64**	**97.20**
2.	2003	እቅድ	595,614,423.97	39,725,937.92	27,000,000	662340361.89
		ክንውን	563,114,773.28	10,988,817.69	16,350,765.86	590454356.83
		ክንውን በመቶኛ	**94.54**	**27.66**	**60.56**	**89.15**
3.	2004 ግመሽ አመት	እቅድ	436,210,700	22,379,700.00	31,616,300.00	490,206,700
		ክንውን	211,335,970.00	16,954,700.00	23,349,880.00	251,640,550
		ክንውን በመቶኛ	**48.45**	**75.76**	**73.85**	**51.33**

ከ2002-2004 ዓመት የገቢ ዕቅድ አፈፃፀም

ተ.ቁ	የበጀት ዓመት		የገቢ ዓይነት በሚሊዮን ብር			ጠቅላላ የፌዴራል መንግሥት ገቢ ድምር
			የአገር ውስጥ ገቢ	የውጭ ንግድ ቀርጥና ታክስ	የብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር የተጣራ ትርፍ	
1.	2002	እቅድ	17,913.85	16,713.05	44.56	34,671.46
		ክንውን	11,381.66	12,172.45	29.15	23,583.26
		በመቶኛ	**63.54 %**	**72.83 %**	**65.42%**	**68.10%**
2.	2003	እቅድ	22,522.57	22,935.04	65.50	45,523.11
		ክንውን	26,160.79	24,581.33	74.33	50,816.45
		በመቶኛ	**116.15 %**	**107.18 %**	**113.48%**	**111.63 %**
3.	2004	እቅድ	40,564.58	35,697.42	107.08	76,367.08
		ክንውን	36,161.58	34,487.65	93.71	70,745.94
		በመቶኛ	**89.15%**	**96.62%**	**90.31%**	**92.64%**

አባሪ 6

የቀረጥና ታክስ ነጻ ንግድ በሚመለከታቸው የስራ ሂደቶች ስር ያሉ ንዑስ የስራ ሂደቶች ዝርዝር

የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም የሥራ ሂደት

121. የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አፈጻጸም የሥራ ሂደት ከስሩ ያሉት የንዑስ ሥራ ሂደቶች፣

- ገቢ አሰበሳብ ንዑስ የሥራ ሂደት ፣
- ገቢ ዕቃዎች አወጣጥ ንዑስ የሥራ ሂደት (ካርጎ ስካኒግ መሽን)፣
- የግል መገልገያ ዕቃዎች የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አፈጻጸ ንዑስ የሥራ ሂደት፣
- በመንግስት የተሰጡ መብቶች የማስፈጸም ንዑስ የሥራ ሂደት፣
- ገቢ ፖስታ ጥቅል ዕቃዎች አፈጻጸም ንዑስ የሥራ ሂደት፣
- የጉምሩክ ስነ-ስርዓት መተላለፍ አጣሪና ውሳኔ ሰጪ ንዑስ የሥራ ሂደት፣
- የወጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ ንዑስ የሥራ ሂደት፣
- የጉምሩክ መጋዘን ንዑስ የሥራ ሂደት፣
- የወጪ ዕቃዎች የጉምሩክ ስነ-ሥርዓት አፈጻጸም ንዑስ የሥራ ሂደት እና የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ንዑስ የሥራ ሂደት ናቸው፡፡

ህግ ማስከበር የሥራ ሂደት

- ህግ ማስከበር የሥራ ሂደት በሥሩ የያዛቸው የንዑስ ሥራ ሂደቶች፤
- የኢንተለጀንስ ሥራ ንዑስ የሥራ ሂደት እና
- ወንጀል ምርመራ ንዑስ የሥራ ሂደት እና ድንገተኛ ፍተሻ ንዑስ የሥራ ሂደት ናቸው፡፡

መንገደኞች ጓዝ የሥራ ሂደት

መንገደኞች ጓዝ የሥራ ሂደት በሥሩ የያዛቸው የንዑስ ሥራ ሂደቶች፣

- የወጪና ገቢ መንገደኞች መስተንግዶ ንዑስ የሥራ ሂደት እና
- የገቢና ወጪ የመንገደኞች አየር ክልል ንዑስ የሥራ ሂደት (አለም አቀፍ ገቢ፤ወጪና አገር ውስጥና አካባቢ በረራ) ናቸው፡፡

የደንበኞች አገልግሎትና ድጋፍ የሥራ ሂደት

የደንበኞች አገልግሎትና ድጋፍ የሥራ ሂደት በሥሩ የያዛቸው የንዑስ ሥራ ሂደት፤

- አጠቃላይ ቅሬታ ማስተናገጃ ንዑስ የሥራ ሂደት፣
- የደንበኞች ትምህርትና ድጋፍ ንዑስ የሥራ ሂደት፣
- የሪከርድ ሥራ አመራር ንዑስ የሥራ ሂደት እና
- የቀረጥ ነጻ ሱቆች ንዑስ የሥራ ሂደት ናቸው፡፡

የድህረ ዕቃ አወጣጥና ኦዲት የሥራ ሂደት

122. የድህረ ዕቃ አወጣጥና ኦዲት የሥራ ሂደት

- የመስክ ኦዲት ንዑስ የሥራ ሂደት እና
- ዴስክ ኦዲት ንዑስ የሥራ ሂደት ናቸው፡፡

አባሪ 7

የቀረጥ ነጻ ንግድ አሠራርና አፈጻጸም የአሠራር ሥርዓት ትንተና (System Description)

ከቀረጥና ታክስ ነጻ ዕቃ ወደ ሀገር ውስጥ ሲገባ የጉምሩክ ስነ ሥርዓት ኮድ(Custom procedure code/CPC) S-702 ተመዝግበው ከወደብ የሚመጡ እና ከአየር መንገድ መጋዘን የሚወጡትን በሲስተም መመዝገብ

↓

ዕቃዎቹ ወደ ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን ይገባሉ

↓

ወደ ቀረጥ ነጻ ዕቃ መሸጫ መደብር አራት ወር ያልሞላቸው ሲተላለፉ አራት ወር የሞላው ቀረጥና ታክስ ተከፍሎበት እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

↓

ቦንድድ የጉምሩክ መጋዘን ከገቡበት ቀን ጀምሮ እስከ አራት ወር ጊዜ ውስጥ የጉምሩክ ስነ ሥርዓት ይፈጸምባቸዋል

↓

ወደ ቀረጥ ነጻ ዕቃ መሸጫ መደብር የገቡ ዕቃዎች ለባለመብቶች ይሸጣል